በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፖብሊክ
የገንዘብ ሚኒስቴር
FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No. ታ/ቁ/ቅ/ፍ/2888

ቀን / Date 27/1/2014

ለገቢዎች ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

የከፍተኛ ግብር ከፋዮች ጽ/ቤት ባቀረበው ጥያቄ መነሻ የአተረጓጐም ችግር በታየባቸው የግብር እና የታክስ ሕግ ድንጋጌዎች ላይ በመ/ቤታችሁ እና በገንዘብ ሚኒስቴር ባለሙያዎች የጋራ ውይይት ተደርጐ ከመግባባት ላይ መደረሱ ይታወቃል፡፡

የግብር እና የታክስ ሕጐች ወጥነት ባለው መንገድ ሥራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ የታክሱን ፍትሐዊነት የሚያስጠብቅ ከመሆኑም በላይ በግብር ከፋዩና በግብር ሰብሳቢው መ/ቤት መካከል የሚፈጠረውን ያለመግባባት በማስቀረት የመንግሥት ገቢ በወቅቱ እንዲሰበሰብ የሚያግዝ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡

በመሆኑም የግብር እና የታክስ ድንጋጌዎችን አፈፃፀም በማብራራት እና ለባለሙያዎች ተከታታይ ሥልጠና በመስጠት አፈፃፀሙ ወጥነት ያለው እንዲሆን የማድረግ ጥረት እንዲቀጥል ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡፡

ስለዚህ በውይይት በተደረሰበት መግባባት መሠረት የተዘጋጀውን ማብራሪያ 40 ገጽ ከዚህ ጋር አባሪ በማድረግ የላክን ስለሆነ የሚመለከታቸው ሁሉ እንዲያውቁት እንዲደረግ እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ኢዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፣
ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
ለታክስ ፖሊሲ ዳይሬክቶሬት
ገንዘብ ሚኒስቴር

Lette.W/GT



በግብር እና በታክስ ሕጐች አፈፃፀም ረገድ በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ የተሰጠ ማብራሪያ

የገንዘብ ሚኒስቴር
መስከረም 2014

ማውጫ

ተራ ቁጥር	ርዕስ	ገጽ
1	<u>የገቢ ግብርን በሚመለከት የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮች</u>	
	1.1 የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወደግል ባለቤትነት በሚዘዋወሩበት ጊዜ የተሸጡበት ዋጋ ለእርጅና ቅናሽ መሠረት ሊሆን ሰለመቻሉ	1
	1.2 የአክሲዮን የትርፍ ድርሻ ስሌት፤	2
	1.3 በድህረ - ዕቃ አወጣጥ አዲት የሚደረስበት ዋጋ፤	3 - 6
	1.4 በዋና መሥሪያ ቤት የተደረገ ወጪ፤	6 - 8
	1.5 ባለኮከብ ሆቴሎች ለሚያገኙት አገልግሎት የሚፈፀም ክፍያ፤	8 - 9
	1.6 ከውጭ አገር ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆኑ ሰዎች የሚሰጥ አገልግሎት፤	9 - 11
	1.7 ሌሎች ገቢዎች፤	11
	1.8 ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር የተያያዙ የታክስ ጥያቄዎች ፤	11 - 12
	1.9 በካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር፤	12 - 15
	1.10 የውጭ ምንዛሪ ጥቅም ወይም ኪሳራ፤	15 - 17
	1.11 በረዥም ጊዜ ውል በተገኘ ገቢ ላይ የሚከፈለው ግብር አወሳሰን፤	17 - 19
	1.12 ለተቀጣሪ ከገበያ ወለድ በታች ብድር በመስጠት የሚገኝ ጥቅም፤	19 - 20
	1.13 ከአርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች ለሚፈፀም ግዥ የሚቀርብ የወጪ ማስረጃ;	20
	1.14 የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት ግብር አከፋፈል	21
	1.15 የክፍያ ስምምነት ውስጥ ያሉ ታክስ ከፋዮች የባንክ ዋስትና ጥያቄ፤	21 - 22
	1.16 ከፍተኛ የአዲት ስጋት ያለባቸው የሚጠየቁት የባንክ ዋስትና፤	22
	1.17 ግብር ከፋዩ ባስታወቀው ገቢ ላይ ማሻሻያ ለማድረግ የሚያቀርበው ጥያቄ	22 - 23
	1.18 ባንኮች የሚይዙት የኪሳራ መጠባበቂያ ሒሳብ፤	23
	1.19 የአንድን ድርጅት ሃብት በአይነት መዋጮነት በማስተላለፍ የሌላ ድርጅት ባለአክሲዮን መሆን	24
	1.20 ኪሳራን ሰለማሸጋገር፤	24 - 25
	1.21 ባንኮች በሌላ ባንክ ገንዘብ በማስቀመጥ የሚያገኙት ወለድ ግብር አከፋፈል፤	25 - 26

ማውጫ

ተራ ቁጥር	ርዕስ	ገጽ
	1.22 የካዝና መጠባበቂያ ገንዘብ፤	26 - 27
	1.23 ወደ ገንዘብ የሚለወጥ የአመት የእረፍት ፈቃድ፤	27
	1.24 በህይወት መድን ስራ ላይ የተሰማሩ ግብር የሚከፈልበት ገቢ፤	28
	1.25 የጋራ ልማት ድርጅት (joint Venutre) የግብር አከፋፈል፤	28 - 29
	1.26 በሳተላይት ቴሌቪዥን አገልግሎት ላይ የሚከፈል ግብር፤	29 - 30
	1.27 በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚሰሩ የውጭ አገር ባለሙያዎች የግብር ነጻ መብት፤	30
	1.28 የግብር አዳ ያለባቸው ታክስ ከፋዮች የሚያቀርቡት የተመላሽ ጥያቄ፤	30 - 31
	1.29 በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ለማሕበራዊ ጉዳዮች የሚሰበሰብ ገንዘብ	31
	1.30 ለጤና ባለሙያዎች የሚፈጸም የተረኝነት የተጋላጭነትና የሌሎች አበሎች ክፍያ፤	31
2.	**<u>የኤክሳይዝ ታክስን በሚመለከት የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮች</u>**	
	2.1 ተመላሽ ለሚደረግ ጠርሙስ የወጣ የትራንስፖርት ወጪ በማምረቻ ወጪ ውስጥ የሚካተት መሆን ያለመሆኑ፤	32
	2.2 ለጠርሙስ መግዣ የወጣ ወጪ አያያዝ፤	32 - 33
	2.3 የኤክሳይዝ ታክስ ደረሰኝ አሰጣጥ፤	33 - 34
	2.4 በግብዓት ላይ የተከፈለ ታክስ ተቀናሽ የሚደረግበት አፈፃፀም	34
	2.5 ለጨርቃጨርቅ ማምረቻ ስለሚውሉ ግብአቶች እና የስፌት አገልግሎት፤	34 - 35
	2.6 በባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ፤	35 36
3	**<u>የተጨማሪ እሴት ታክስን በሚመለከት የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮች</u>**	
	3.1 በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው የሚሰጥ አገልግሎት፤	35
	3.2 ከቀረጥ ነጻ ለሚገባ ተሽከርካሪ የሚከፈል ኮሚሽን፤	36
	3.3 በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት ሲሸጥ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ የሚደረግበት ሁኔታ፤	37 - 38
4	**የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 85 (ስህተትን ሰለማረም)፤**	38 - 39

በግብርና በታክስ ሕጐች አፈፃፀም ረገድ
ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጠ ማብራሪያ

በአንዳንድ የግብር አና የታክስ ሕጐች አተረጓጐም ረገድ በባለሙያዎች መካከል የሀሳብ ልዩነት ያለ ሲሆን፣ ይህ የሀሳብ ልዩነት በአንድ ጉዳይ ላይ የተለያየ የግብር ውሣኔ እንዲሰጥ በማድረግ የታክሱን ፍትሐዊነት የሚያዛባ ከመሆኑም በላይ በአተረጓጐም ምክንያት ከግብር ከፋዩ ጋር የሚፈጠረው ያለመግባባት ጉዳዮች ወደ ክርክር እንዲያመሩ በማድረግ ለመንግሥት ገቢ መዘግየት ምክንያት ሲሆን ይታያል።

ይህም በመሆኑ የታክስ ሕጐች አፈፃፀም ወጥነት ያለው እንዲሆን ለማድረግ እንዲሁም በየጊዜው በሚያጋጥመው የአተረጓጐም ልዩነት ምክንያት የሚፈጠረው ክርክር በገቢ አሰባሰብ ላይ የሚያስከትለውን መዘግየት ለማስቀረት በተደጋጋሚ ጥያቄ በሚቀርብባቸው ጉዳዮች ላይ የሚከተለው ማብራሪያ ተዘጋጅቷል።

1. <u>የገቢ ግብርን በሚመለከት የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮች</u>

1.1 <u>የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወደግል ባለቤትነት በሚዘዋወሩበት ጊዜ የተሸጡበት ዋጋ ለእርጅና ቅናሽ መሠረት ሊሆን ስለመቻሉ</u>

የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ወደግል በሚዘዋወሩበት ጊዜ በጨረታ መነሻ እና በተሸጡበት ዋጋ መካከል ያለውን ልዩነት አንዳንድ ድርጅቶች የመልካም ዝና (good will) ዋጋ አድርገው በመመዝገብ ወጪውን በአመታት ከፋፍለው በመያዝ አሞርታይዝ የሚያደርጉ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ደግሞ የሸያጩን ዋጋ ለድርጅቱ ንብረቶች የመዝገብ ዋጋ በማከፋፈል የእርጅና ቅናሽ እንዲሰላበት ያደርጋሉ።

የመንግሥት የልማት ድርጅቶችን ወደግል ስለማዛወር የወጣው አዋጅ ቁጥር 1206/2012 አንቀጽ 14 ወደግል ይዞታ የተዘዋወረ የመንግሥት የልማት ድርጅት ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚሠላበት ጊዜ የእርጅና ቅናሽ ስሌት መሠረት የሚሆነው የጨረታው መነሻ ዋጋ መሆኑን፣ ሆኖም የጨረታው መነሻ ዋጋ ያነሰ ከሆነ ገዥው በከፈለው ትክክለኛው የገንዘብ መጠን ላይ ተመስርቶ የእርጅናው ቅናሽ ስሌት መከናወን እንደሚገባው ይደነግጋል።

ለዚህ የአዋጁ ድንጋጌ አፈፃፀም እንዲያመች የመንግሥት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ የንብረቶቹን ዋጋ ዝርዝር ለታክሱ ባለሥልጣን ማቅረብ እንደሚገባው የአዋጁ አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 2 በተጨማሪ ደንግጓል።

በመሆኑም ወደግል ባለቤትነት የተዘዋወሩ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የእርጅና ቅናሽ መሠረት የሚሆነው ገዥው የከፈለው ትክክለኛው ዋጋ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ንብረት የተሸጠበትን ዋጋ ዝርዝር ኤጀንሲው ለታክሱ ባለስልጣን መላክ ይኖርበታል።

1.2 <u>የአክሲዮን የትርፍ ድርሻ ስሌት</u>

የአክሲዮን የትርፍ ድርሻ ግብር መሠላት ያለበት በገቢ ግብር አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት በተስተካከለው የግብር ከፋዩ የተጣራ ትርፍ ላይ ነው ወይስ ማስተካከያ ከመደረጉ በፊት በግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ ላይ በታየው ትርፍ ላይ ነው? የሚል የሀሳብ ልዩነት ይንፀባረቃል።

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀጽ 52 አንድ ድርጅት ለባለሥልጣኑ ያሳወቀው የንግድ ሥራ ትርፍ መጠን ባለሥልጣኑ ባደረገው አዲት ከደረሰበት ግኝት ያነሰ መሆኑ ድርጅቱ ባሳወቀው ትርፍ ላይ ተመስርቶ ለባለአክሲዮኖች ባከፋፈለው የትርፍ ድርሻ ላይ በተከፈለው ግብር ላይ ውጤት እንደማይኖረው ይደነግጋል።

የንግድ ሥራ ድርጅት ለንግድ ሥራው ገቢ ለማስገኘት ከሚያወጣቸው ወጪዎች መካከል ለግብር አከፋፈል ሲባል ተቀናሽ የማይደረጉ እንዳሉ ይታወቃል። እነዚህ ወጪዎች ለግብር አከፋፈል ሲባል ተቀናሽ የማይደረጉ ቢሆንም ድርጅቱ ለንግድ ስራው ይጠቅማል በሚል አላማ ገንዘቡን ወጪ ያደረገ በመሆኑ ለባለአክሲዮኖች የሚከፋፈለው የትርፍ ድርሻ ይህንን ወጪ ሳይጨምር ድርጅቱ ያገኘው ትርፍ እንደሚሆን ግልፅ ነው። በዚህም ምክንያት ከላይ የተጠቀሰው የገቢ ግብር ደንብ ድንጋጌ ተቀናሽ በማይደረጉ ወጪዎች ምክንያት በግብር ከፋዩ የሂሳብ መዝገብ ላይ የተደረገው ማስተካከያ በትርፍ ድርሻ (ዴቪደንድ) ላይ ለሚከፈለው ግብር ውጤት እንደማይኖረው በግልፅ ደንግጓል።

በመሆኑም በአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ላይ የሚከፈለው ግብር መሰላት ያለበት ግብር ከፋዩ በሂሳብ መዝገቡ መሠረት ለባለአክሲዮኖች ባከፋፈለው የትርፍ ድርሻ ላይ እንጂ በተስተካከለው የሂሳብ መዝገብ መሠረት ሊሆን አይገባም።

ይሁን እንጂ ግብር ከፋዩ የተጭበረበረ ማስረጃን በመጠቀም የደበቀው ገቢ በመኖሩ ወይም ሐሰተኛ የወጪ ማስረጃ በማቅረቡ ውድቅ የተደረገ ወጪ ወይም የተስተካካለ ገቢ ካለ እነዚህ ድርጊቶች የወንጀል ውጤት በመሆናቸው በዚህ ረገድ የሚደረጉ ማስተካከያዎች በአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ግብር ላይ ውጤት እንደሚኖራቸው ሊታወቅ ይገባል።

በሌላ በኩል አንዳንድ ግብር ከፋዮች በኦዲት እና በስሌት ልዩነት ምክንያት ተጨማሪ ታክስ፤ ወለድ እና መቀጫ እንዲከፍሉ ሲደረግ ይህንን ሂሳብ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻ መሰረት ከሆነው የተጠራቀመ ትርፍ ላይ በመቀነስ እና ትርፋቸው እንዲቀንስ ወይም ዜሮ እንዲሆን በማድረግ በአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ላይ ተገቢውን ግብር አይከፍሉም የሚል ሃሳብ ይነሳል።

የንግድ ሕግ አንቀጽ 432 የአንድ ማህበር የተጣራ ትርፍ የሚባለው የማህበሩ ጠቅላላ ወጪዎች እንዲሁም የአላቂ ንብረቶች መተኪያ ገንዘብና የእርጅና ቅናሽ ሂሳብ ከተቀነሰ በኋላ የሚገኘው ትርፍ መሆኑን ይገልጻል።

በመሆኑም እነዚህን ወጪዎች ኩባንያው በትክክል ወጪ ያደረገ በመሆኑ ለባለአክሲዮኖች ሊከፋፈል የሚችለው ወጪዎቹ ተቀንሰው የሚቀረው ትርፍ መሆኑ ግልጽ ነው። በአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ላይ ግብር የሚከፈለው ደግሞ በተከፋፈለ ወይም ሊከፋፈል በሚችል ገቢ ላይ ነው። መቀጫን በተመለከተ የገቢ ግብር አዋጁ በወጪነት አይያዝም ያለው የንግድ ትርፍ ግብር በሚሰላበት ጊዜ ነው። በመሆኑም እነዚህ ወጪዎች ከተጠራቀመ ትርፍ ላይ መቀነሳቸው ተገቢ ነው።

1.3 <u>በድህረ - ዕቃ አወጣጥ አዲት የሚደረስበት ዋጋ</u>

በጉምሩክ አዋጅ ቁጥር 859/2006 በተደነገገው መሠረት አስመጪው ወደአገር ላስገባው ዕቃ ያቀረበውን ዲክላራሲዮን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የጉምሩክ ኮሚሽን የድህረ - ዕቃ አወጣጥ አዲት ሊያከናውን ይችላል። በድህረ - ዕቃ አወጣጥ አዲት አስመጪው ወደአገር ያስገባው ዕቃ ዋጋ ከገበያው ዋጋ አንሶ ወይም ከፍ ብሎ በሚገኝበት ጊዜ ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ እንዲከፍል የሚደረግ ሲሆን፣ የጉምሩክ ኮሚሽን መረጃው ለአገር ውስጥ ታክስ አወሳሰን እንዲያግዝ ይልካል።

ጥያቄ ሆኖ የቀረበው የድህረ - አቃ አወጣጥ አዲት የሚከናወነው ከዓመታት በኋላ በመሆኑ በአዲት ግኝቱ የዕቃው ዋጋ አንሷል ወይም ከፍ ብሏል የሚባልበት ጊዜ ግብር ከፋዩ ዕቃውን ለግብይት ካዋለው ከዓመታት በኋላ ሊሆን ስለሚችል ግብር ከፋዩን የንግድ ትርፍ ግብር ወይም የተጨማሪ እሴት ታክስ መጠየቅ ይቻላል ወይ? በሌላ በኩል የአዲት ግኝቱ ግብር ከፋዩ ተጨማሪ ታክስ እንዲከፍል የሚያስገድድ ቢሆን፣ ታክስ ከፋዩ ለጉምሩክ ኮሚሽን የከፈለው ታክስ እንዲመለስለት ወይም በወጪ እንዲያዝለት ቢጠይቅ በመንግሥት ላይ ወጪን ሊያስከትል ስለሚችል ጉዳዩ በምን አኳኋን ሊመራ ይገባል? የሚል ነው።

በጉምሩክ አዋጅ አንቀጽ 90 የግብይት ዋጋ (transaction value) የሚወሰንባቸው ሁኔታዎች በግልፅ ተደንግገዋል። በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(መ) ገዥውና ሻጩ ግንኙነት ያላቸው ከሆነ የግብይት ዋጋው የቀረጥና ታክስ መተመኛ ዋጋ ሆኖ የሚወሰደው በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ሲያገኝ እንደሆነ ተመልክቷል። በመሆኑም በአንቀፁ የሰፈሩ ሌሎች ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆነው የጉምሩክ ኮሚሽን የግብይት ዋጋ ተቀባይነት እንዲያጣ ሊያደርግ የሚችለው በአስመጪው እና በሻጩ መካከል ግንኙነት ያለ መሆኑን ሲያረጋግጥ ሊሆን ይገባል።

የጉምሩክ ኮሚሽን በገዥውና በሻጩ መካከል ግንኙነት ያለ መሆኑን በማረጋገጥ የዕቃውን ዋጋ (ኢንቮይስ) ውድቅ ሲያደርግ ባለው መረጃ ላይ ተመስርቶ የቀረጥና ታክስ መተመኛውን ዋጋ ሊወስን ይችላል።

በሌላ በኩል የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 3 አዋጁ ተፈፃሚ ለሚሆንባቸው ታክሶች (የገቢ ግብር፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የኤክሳይዝ ታክስ፣ የቴምብር ቀረጥ፣ የተርንኦቨር ታክስ) ዓላማ የአንድ ዕቃ፣ ንብረት፣ አገልግሎት ወይም ጥቅም ትክክለኛ የገበያ ዋጋ ነው የሚባለው የዕቃው፣ የንብረቱ፣ የአገልግሎቱ ወይም የጥቅሙ የወቅቱ እና የቦታው መደበኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን የሚገልፅ ሲሆን፣ ትክክለኛውን የገበያ ዋጋ ማወቅ ካልተቻለ ማስተካከያ የሚደረግበትን ሥርዓት ይዘረጋል። በተጨማሪም የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 3 ስለማሸጋገሪያ ዋጋ (transfer pricing) በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 79 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማለትም ግብይቱ የተከናወነው ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል በሚሆንበት ጊዜ የዕቃው ዋጋ በአንቀጽ 3 ከንዑስ አንቀጽ 2 - 6 በተዘረዘረው መሠረት የሚወሰን መሆኑን ይደነግጋል።

በመሆኑም ለገቢ ግብር አዋጅ አፈፃፀምም ግብር ከፋዩ ያቀረበው ዋጋ ተቀባይነት ሊያጣ የሚችለው ግብይቱ የተከናወነው ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል ሲሆን ነው።

እነዚህ የሕጎቹ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው የጉምሩክ ኮሚሽን በድህረ - ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ግኝት ግብይቱ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል መከናወኑን አረጋግጦ የዕቃው ዋጋ በዲክላራሲዮን ከተመለከተው ያነሰ ወይም የበለጠ መሆኑን በሚገልፅበት ጊዜ ይህ መረጃ ለገቢ ግብር እና ለተጨማሪ እሴት ታክስ አወሳሰን በምን መልኩ ሊያገለግል ይችላል? የሚለው ምላሽ ሊያገኝ ይገባል። በመሆኑም እነዚህን ውስብስብ የሆኑ የአሠራር ችግሮች ለማስቀረት በድህረ - ዕቃ አወጣጥ ኦዲት የሚገኘው የጉምሩክ መረጃ ለአገር ውስጥ ታክሶች አወሳሰን በምን መልክ ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል መወሰን አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

አስመጪው ወደአገር ባስገባው ዕቃ ላይ ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ ዕቃውን ለሽያጭ ካዋለ ከዓመታት በኋላ የዕቃው ዋጋ በዲክላራሲዮን ከተገለፀው በላይ ነው ሲባል የዕቃውን ዋጋ አስተካክሎ ዕቃውን ለገበያ የሚያውልበት ዕድል አይኖርም። ከዚህም በላይ ዕቃውን ለገበያ ያዋለበት ዋጋ በተጨማሪ እሴት ታክስ ኢንቮይስ ላይ የተመለከተ በመሆኑ በጉምሩክ ኮሚሽን ወደአገር በገቡት ዕቃዎች አዲሱ ዋጋ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ እንዲከፍል ሲደረግ ለጉምሩክ ኮሚሽን የተከፈለው ታክስ ዕቃዎቹ በተሸጡበት ጊዜ ከተሰበሰበው ሊበልጥ ስለሚችል የተመላሽ ጥያቄ ሊያቀርብ እንዲሁም በገቢ ዕቃዎች ላይ አዲስ የከፈለው ቀረጥና ታክስ እንደወጪ እንዲያዝለት ሊጠይቅ ይችላል።

የጉምሩክ መረጃ በአገር ውስጥ ታክሶች አወሳሰን ረገድ ለሽያጭ ለሚውሉ ዕቃዎች (trading stock) እና ለቋሚ ንብረቶች (fixed assets) ዋጋ አወሳሰን ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። ለሽያጭ የሚውሉ ዕቃዎችን በሚመለከት ታክስ ከፋዩ ወደአገር ያስገባውን ዕቃ ለገበያ ካዋለ ከዓመታት በኋላ የዕቃውን ዋጋ ጉምሩክ ከፍ አድርጐ ሲወስን አስመጪው ተጨማሪ ቀረጥና ታክስ እንዲከፍል ይገደዳል። ይሁን እንጂ የድህረ - ዕቃ አወጣጥ አዲቱ የሚከናወነው አብዛኛውን ጊዜ ዕቃው ከተሸጠ ከበርካታ ዓመታት በኋላ በመሆኑ ከላይ እንደተገለፀው ታክስ ከፋዩ ይህንን ዋጋ እና የከፈለውን ቀረጥና ታክስ መሠረት አድርጐ ዕቃውን ለገበያ ሊያውል የሚችልበት ዕድል አይኖርም።

በመሆኑም ታክስ ከፋዩ በብልጫ የከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ እንዲደረግለት ጥያቄ ሊያቀርብ ስለሚችል በድህረ - ዕቃ አወጣጥ አዲት የተገኘው መረጃ ለተጨማሪ እሴት ታክስ አወሳሰን ከግምት ውስጥ እንዲገባ ማድረግ ተገቢ አይሆንም። የተመላሽ ጥያቄው የሚቀርበው በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ የተመላሽ ጥያቄ ለማቅረብ ከተወሰነው ጊዜ በኋላ በመሆኑ የተመላሽ ጥያቄው የሕግ አግባብነት አይኖረውም ቢባልም ግብር ከፋዩ ለከፍተኛ ኪሳራ ይጋለጣል።

የገቢ ግብርን በተመለከተ አስመጪው ወደአገር ያስገባቸው ዕቃዎች ዋጋ ከገበያ ዋጋ በላይ ወይም ከገበያ ዋጋ በታች መሆኑ ሊረጋገጥ ይችላል። ከገበያ ዋጋ በታች በመሆኑ ዋጋው ከፍ ተደርጐ ሲወሰን ለግብር አከፋፈል የወጪው መጠን በዚያው መጠን ከፍ እንዲል፤ ገቢውም በዚያው መጠን እንዲጨምር መደረግ አለበት የሚል ጥያቄ ይነሳል። የቋሚ ንብረቶች ዋጋ ከፍ ተደርጐ የነበረ በመሆኑ በድህረ - ዕቃ አወጣጥ አዲት ዝቅ ተደርጐ ቢወሰን ደግሞ የእርጅና ቅናሽ ሊሰላ የሚገባው በየትኛው ዋጋ ላይ ነው? የሚል ጥያቄ ይነሳል።

በገቢ ግብር አዋጅ እንደተደነገገው ማናቸውም ወጪ በተቀናሽነት ሊያዝ የሚችለው ገቢውን ለማመንጨት የዋለ በሚሆንበት ጊዜ ነው። በድህረ - ዕቃ አወጣጥ አዲት አስመጪው ከዓመታት በኋላ የሚከፍለው ቀረጥና ታክስ ከዓመታት በፊት ያገኘውን ገቢ ለማመንጨት የዋለ ባለመሆኑ ተቀናሽ እንዲደረግ መፍቀድ አስቸጋሪ ይሆናል። በመሆኑም የዕቃው ዋጋም ሆነ በዚህ መልክ የተከፈለው ቀረጥና ታክስ በወጪም ሆነ በገቢ እንዲያዝ ማድረግ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም። ይሁን እንጂ ታክስ ከፋዩ የሚከፍለውን ቀረጥ እና ታክስ በሂሳቡ ውስጥ መመዝገቡ ስለማይቀር በተጠራቀመ ትርፍ ላይ ማስተካከያ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።

አስመጪው እና ሻጩ ግንኙነት ያላቸው (ግብይቱ የተፈፀመው ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል) በመሆኑ ምክንያት ወደአገር የገባው ቋሚ ንብረት ዋጋ የተጋነነ ሆኖ ከተገኘ የእርጅናው ቅናሽ መሠረት ሊሆን የሚገባው ትክክለኛው የገበያ ዋጋ መሆን

አለበት፡፡ በመሆኑም የታክሱ ባለሥልጣን ከጉምሩክ ኮሚሽን ወይም ከማናቸውም ሌላ የመረጃ ምንጭ የሚያገኘውን መረጃ መሠረት በማድረግ የእርጅና ቅናሹን መሠረት ሊወስን ይችላል፡፡ ሻጩና ገዥው ግንኙነት ያላቸው መሆኑ ካልተረጋገጠ ግን ለእርጅና ቅናሽ መሠረት ሊሆን የሚገባው ዕቃው የተገዛበት ኢንቮይስ መሆን አለበት፡፡

በተደጋጋሚ እንደተገለፀው በጉምሩክ አዋጅ፣ በገቢ ግብር አዋጅ እና በታክስ አስተዳደር አዋጅ መሰረት የታክሱ ባለሥልጣን በግብይቱ ኢንቮይስ ላይ የተመለከተውን ዋጋ ሊያስተካክል የሚችለው ግብይቱ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የተከናወነ በሚሆንበት ጊዜ ነው፡፡ በመሆኑም በድህረ እቃ አወጣጥ አዲት የተገኘው መረጃ ግብይቱ ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል መሆኑን ካላረጋገጠ ግብር ከፋዩ ያቀረበውን ቋሚ ንብረቱ የተገዛበትን ዋጋ ውድቅ ማድረግ ተገቢ አይሆንም፡፡

ሻጩና ገዥው ግንኙነት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ በዋጋ ማሸጋገሪያ መመሪያ ቁጥር 43/2007 በተመለከተው መሰረት የሻጩንና የገዥውን ኩባንያዎች የመመስረቻ ፅሑፍ በማስቀረብ የኩባንያዎችን ባለቤቶች ማንነት ማወቅ አንዱ ጠቃሚ መረጃ ነው፡፡

1.4 <u>በዋና መሥሪያ ቤት የተደረገ ወጪ</u>

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠሩ የውጭ አገር ኩባንያዎች በዋና መሥሪያ ቤታቸው አማካኝነት ለተሰጣቸው አገልግሎት የከፈሉት ክፍያ እንዲሁም በዋናው መ/ቤት በኩል ለተፈፀመላቸው ግዢ ያወጡት ወጪ እንዲያዝላቸው በሚጠይቁበት ጊዜ ወጪው የተጋነነ ነው በሚል ምክንያት ውድቅ ስለሚደረግ በታክስ ከፋዩና በግብር ሰብሳቢው መ/ቤት መካከል ከፍተኛ ያለመግባባት ይፈጠራል፡፡

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 22 እንደተመለከተው በንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ የተካተቱትን ገቢዎች ለማግኘት፣ ለንግዱ ሥራ ዋስትና ለመስጠትና የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል የተደረጉ ወጪዎች የግብር ከፋዩ ግብር የሚከፈልበት ገቢ በሚወሰንበት ጊዜ በወጪነት ተቀናሽ ይደረጋሉ፡፡ በወጪነት ተቀናሽ የማይደረጉት በአዋጁ አንቀጽ 27 የተዘረዘሩ ወጪዎች ብቻ ናቸው፡፡

ይህንን የአዋጁን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀጽ 35 በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት ለሚሠራው ድርጅቱ ጥቅም ያደረገውን ትክክለኛ ወጪ ለመተካት በኢትዮጵያ ውስጥ በቋሚነት የሚሠራው ድርጅት የሚፈፅመው ክፍያ ለንግድ ሥራው ገቢ ለማስገኘት፣ ለንግዱ ሥራ ዋስትና ለመስጠት ወይም የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል እስከሆነ ድረስ ተቀናሽ እንደሚደረግ ይገልፃል፡፡

ይሁን እንጂ በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 79 እንደተደነገገው በዋናው መሥሪያ ቤት እና በኢትዮጵያ ውስጥ በሚሠራው ዘላቂ ድርጅት መካከል የሚደረገው ግብይት ወይም ለዋናው መ/ቤት የተፈፀመ ክፍያ በገበያ መርህ የተደረገ መሆን አለበት። በገበያ መርህ ያልተፈፀመ (የተጋነነ) ከሆነ የታክሱ ባለሥልጣን በእነዚህ ወጪዎች ላይ ማስተካከያ ሊያደርግ ይችላል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ የውጭ አገር ኩባንያዎች ለዋናው መ/ቤት የተለያዩ ክፍያዎችን የሚፈፅሙ ሲሆን፣ በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙት የጠቅላላ አገልግሎት ክፍያ (general administrative expense)፣ የግዥ ኮሚሽን (Buying commission)፣ የሥልጠና ወጪ (በበይነ መረብ የሚሰጠውን ጨምሮ)፣ የምክር አገልግሎት (advisory support)፣ የሮያልቲ/የዕውቀት ሽግግር ክፍያ በመባል የሚታወቁት ናቸው።

ከዚህ በላይ እንደተገለፀው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠሩ የውጭ አገር ኩባንያዎች ለዋና መሥሪያ ቤታቸው የሚፈፅሙት ገቢውን ለማግኘት ሲባል የወጣ ወጪ በመሠረተ - ሀሳብ ደረጃ በተቀናሽነት የሚያዝ ቢሆንም፣ ወጪው ተቀባይነት የሚኖረው፣

- አገልግሎቱ በትክክል የተሰጠ ወይም ዕቃው በትክክል የቀረበ መሆኑን፤
- ተከናወነ የተባለው ሥራ ወይም የውጭ ባለሙያ ድጋፍ ያስፈለገው የሥራ ዓይነት/ሥልጠና ኩባንያው በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉት ሠራተኞች ወይም በአገር ውስጥ ሊከናወን የማይችል መሆኑን፣
- ዋናው መሥሪያ ቤት በመላው ዓለም ለሚገኙ ቅርንጫፎቹ የሚሰጠው የድጋፍ አገልግሎት ከሆነ፣ የዚህ ዓይነቱ ወጪ ለቅርንጫፎች የሚከፋፈልበትን የዋናውን መ/ቤት ፖሊሲ እንዲሁም ኩባንያው ለድጋፍ አገልግሎት ያወጣው ወጪ የቅንጫፎችን የሥራ እንቅስቃሴ መሠረት በማድረግ በተገቢው መንገድ የተከፋፈለ መሆኑን፣
- ዋናው መ/ቤት በኢትዮጵያ ለሚገኘው ቅርንጫፍ የገዛው ዕቃ ዋጋ ክፍያ የተፈፀመ ከሆነ የተገዛው ዕቃ ዋጋ ትክክለኛ የገበያ ዋጋ መሆኑን፣
- በኢትዮጵያ ያለው ቅርንጫፍ በሦስተኛ ወገን የፈጠራ መብት የሚጠቀም በመሆኑ ምክንያት የሚከፈል የሮያልቲ ክፍያ ከሆነ ዋናው መ/ቤት ለሦስተኛ ወገን ከፈፀመው ክፍያ ውስጥ በኢትዮጵያ ላለው ቅርንጫፍ የተደለደለው የቅርንጫፉን የሥራ እንቅስቃሴ መሠረት ባደረገ አኳኋን መሆኑን፣

- ዋናው መ/ቤት ለሚፈፅመው ግዥ ኮሚሽን የሚከፈል ከሆነ፣ የኮሚሽኑ መጠን በአገር ውስጥ በሚገኙ ኩባንያዎች ከሚፈፀም የኮሚሽን ክፍያ ያልበለጠ መሆኑን፣

በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ኩባንያ ማስረዳት ሲችል ብቻ መሆን አለበት።

ከዚህ በላይ እንደተመለከተው ዋናው መሥሪያ ቤት ለሶስተኛ ወገኖች የሚፈጽመው የሮያልቲ ክፍያ ካለ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሰብሲዲየሪ በዚህ የሮያልቲ መብት የሚጠቀም ከሆነ በተጠቀመው መጠን ለዋናው መሥሪያ ቤት የሚፈጽመው የሮያልቲ ክፍያ እንዲሁም ግንኙነት ለሌለው ሦስተኛ ወገን በቀጥታ የሚፈጽመው የሮያልቲ ክፍያ በወጪነት ይያዛል። ዋናው መስሪያ ቤት ለራሱ የፈጠራ መብት ከቅርንጫፉ ወይም ሰብሲዲየሪው የሚጠይቀው የሮያልቲ ክፍያ ቢኖር ግን ተቀናሽ ሊደረግ አይችልም

በአጠቃላይ ለዋና መ/ቤት የሚፈፀሙ ክፍያዎች ግንኙነት ባላቸው ሰዎች መካከል የሚፈፀሙ እንደመሆኑ ለማሸጋገሪያ ዋጋ (transfer pricing) የተጋለጡ ስለሚሆን የግብይቱ ዋጋ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል ከሚደረገው (arm's length) ያልበለጠ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል።

በዚህም መሠረት ስለማሸጋገሪያ ዋጋ በወጣው መመሪያ ቁጥር 43/2007 የዚህ ዓይነቱን ድርጊት ለመቆጣጠር የተዘረጋውን ሥርዓት መሠረት በማድረግ የግብይቱን ዋጋ ከሌሎች ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል ከተደረጉ ተመሳሳይ ግብይቶች ጋር በማነፃፀር የዋጋውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አስፈላጊ ይሆናል።

ለማጠቃለል በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ኩባንያዎች ከዋና መ/ቤታቸው ለሚያገኙት አገልግሎት ወይም ለሚቀርብላቸው ዕቃ የሚፈፅሙት ክፍያ የንግድ ሥራውን ለማስቀጠል እስከሆነ ድረስ ተቀናሽ መደረግ ያለበት ሲሆን፣ አፈጻፀሙ ከዚህ በላይ የተመለከተውን አሠራር ሊከተል ይገባል።

1.5 <u>ባለኮከብ ሆቴሎች ለሚያገኙት አገልግሎት የሚፈፀም ክፍያ</u>

ባለኮከብ ሆቴሎች በአመዛኙ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ ዝና ባላቸው የሆቴል ኩባንያዎች አስተዳደራቸው የሚመራ በመሆኑ የአስተዳደሩን ሥራ ለሚያከናውነው ዓለም ዐቀፍ የሆቴል ኩባንያ የተለያዩ ክፍያዎችን ይፈፅማሉ። እነዚህ ዓለም ዐቀፍ ሆቴሎች ከሆቴሉ ባለቤት ጋር ግንኙነት ያላቸው ቢሆንም ባይሆንም የክፍያው ዓይነት፣ የክፍያው መሠረት እና መጠኑ የተለያየ መሆኑ ለክርክር በር ይከፍታል።

የሆቴል አስተዳደሩን ሥራ የሚያከናውኑት አንዳንድ ኩባንያዎች ለሚሰጡት አገልግሎት ሆቴሉ ከሚያገኘው ትርፍ የተወሰነ መቶኛ የሚያገኙ ሲሆን፣ የተቀሩት ደግሞ ከጠቅላላ የሆቴሉ የሽያጭ ገቢ ላይ የተወሰነ መቶኛ ያገኛሉ፣ ከዚህም በተጨማሪ የማስታወቂያ ወጪ እየተባለ ከሽያጩ ገቢ የተወሰነ መቶኛ (እስከ 3.9%) ለአገልግሎት ሰጪዎች ይከፈላል። የዚህ ዓይነቶቹ ትርፍን መሠረት ያላደረጉ ክፍያዎች የሆቴሉን ትርፍ በከፍተኛ ደረጃ ስለሚቀንሱ ሆቴሎቹ አብዛኛውን ጊዜ ኪሣራ ሪፖርት የሚያደርጉ ሲሆን፣ ግብር የሚከፍሉ ቢሆንም የግብሩ መጠን ከሥራው እንቅስቃሴ ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ነው።

ትርፍን መሠረት ያላደረጉ የተጋነኑ የአገልግሎት ክፍያዎች አንዳንድ ጊዜ ካፒታል ለማሸሽ ጭምር ሊውሉ ስለሚችሉ የዚህ ዓይነቱን ህገወጥ ድርጊት ለመከላከል ወጥ የሆነ አሠራር መዘርጋት ግድ ይሆናል።

በመሆኑም የገንዘብ ሚኒስቴር በገቢ ግብር አዋጅና በሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የሆቴሎችን የመዋዋል ነፃነት ባልገደበ ሁኔታ ለዚህ ዓይነቱ ወጪ ጣሪያ እንዲያበጅ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። በዚህም መሠረት ሆቴሉ ትርፍን ወይም ጠቅላላ ሽያጭን መሠረት በማድረግ ከዓለም ዐቀፍ የሆቴል አገልግሎት ሰጪዎች ጋር የመዋዋል መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአገልግሎት ክፍያው ትርፍን መሠረት ያደረገ ከሆነ ከጠቅላላው ትርፍ ውስጥ በሚኒስቴሩ ከሚወሰን መቶኛ ያልበለጠ እንዲሁም ጠቅላላ ሽያጭን መሠረት ያደረገ ሲሆን ከጠቅላላው ሽያጭ ውስጥ በሚኒስቴሩ ከሚወሰን መቶኛ ያልበለጠው ብቻ ተቀናሽ እንደሚደረግ በግልፅ መወሰን ያስፈልጋል።

የዚህ ዓይነቱ ጣሪያ የማበጀት አሠራር ከባለአክሲዮኖች ለሚወሰድ ብድር በሚከፈል ወለድ፣ ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ወ.ዘ.ተ. ላይ በተመሳሳይ የሚፈፀም በመሆኑ ከሕጉ ጋር የሚጣጣም ነው። በመሆኑም የገንዘብ ሚኒስቴር በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 99(2) በተሰጠው አጠቃላይ ስልጣን መሰረት ለማስታወቂያ የሚወጣውን ወጪ ጣሪያ በመመሪያ ሊወሰን ይገባል።

1.6 <u>ከውጭ አገር ወይም የኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆኑ ሰዎች የሚሰጥ አገልግሎት</u>

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚሠሩ የውጭ አገር ኩባንያዎች እንዲሁም የኢትዮጵያ ኩባንያዎች ከውጭ አገር ከሦስተኛ ወገኖች ለሚያገኙት አገልግሎት የሚፈፅሙት ክፍያ እንዲሁም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚሰጡት አገልግሎት በሚያገኙት ገቢ ላይ ግብር የሚከፈልበት እና ወጪው ተቀናሽ የሚደረግበት አካኋን ሌላው ለክርክር የተጋለጠ ጉዳይ ነው።

የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 7 በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎችን በተመለከተ አዋጁ ተፈጻሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያገኙት ገቢ ላይ መሆኑን ይገልጻል። በኢትዮጵያ ነዋሪ ስላልሆኑ ሰዎች ገቢ የሚያብራራው የአዋጁ አንቀጽ 51፤ 52፤ 53፤ 54፤ 55፤ 56 እና 62 በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው የትርፍ ድርሻ፤ወለድ፤ ሮያልቲ፤ የስራ አመራር ክፍያ፤ የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ፤ የመድን አረቦን፤የመዝናኛ አገልግሎት ክፍያ ፤ ወደውጭ የሚላክ ትርፍ ከኢትዮጵያ ውስጥ ያገኘ እንደሆነ በዚሁ አንቀጽ በተመለከተው መጣኔ መሰረት ግብር ሊከፈልበት እንደሚገባ ያመለክታል። በመሆኑም ከኢትዮጵያ ውጭ የሚኖሩ ሰዎች ግብር የሚከፍሉት ከዚህ በላይ በተዘረዘሩት ገቢዎች ላይ ነው። ከነዚህ ገቢዎች መካከል የትርፍ ድርሻ፤ ወለድ፤ ሮያልቲ፤ የስራ አመራር ክፍያ እና የቴክኒክ አገልግሎት በአዋጁ ተተርጉመዋል። ለምሳሌ የቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ በአዋጁ አንቀጽ 2 (24) እንደተተረጎመው ለቴክኒካዊ፤ ሙያዊ ወይም ለማማከር አገልግሎት የሚከፈል ክፍያ ሲሆን፤ የቴክኒክ ወይም ሌሎች ባለሙያዎችን ለመጠቀም የሚከፈል ክፍያን ይጨምራል። በመሆኑም የቴክኒክ አገልግሎት የሚባለው የሰውን ልጅ እውቀት በመጠቀም የሚሰጥ አገልግሎት ሲሆን፤ ከዚህ ውጪ ያለውን አይጨምርም።

ከኢትዮጵያ ውጪ ሆኖ የሚሰጠውን አገልግሎት የጊዜ ቆይታ በማየት 30% ግብር ሊከፈልበት ይገባል የሚል አስተያየት ይቀርባል። ይሁን እንጂ የገቢው ባለቤት በኢትዮጵያ ነዋሪ እስካልሆነ ድረስ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነው ድርጅት በኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ድርጅት ያለው እስካልሆነ ድረስ ከኢትዮጵያ ውጪ ሆኖ የሚሰጥ አገልግሎት በጊዜ ገደብ የሚለካ ባለመሆኑ ግብሩ የሚከፈለው በአንቀጽ 51 በተመለከተው መጣኔ ብቻ ነው።

በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 92 (4) እና በገቢ ግብር ደንብ አንቀጽ 63 በተደነገገው መሠረት አቅራቢው/አገልግሎት ሰጪው የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የንግድ ፈቃድ ሊያቀርብ ካልቻለ አገልግሎቱን ያገኘው ሰው ከሚከፍለው ገንዘብ ላይ 30% ግብር ቀንሶ ማስቀረት አለበት የሚሉትን ድንጋጌዎች መሰረት በማድረግ 30% ግብር እንዲከፍሉ ይጠየቃል።በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች እና በኢትዮጵያ ዘላቂ ድርጅት ያላቸው ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የንግድ ፈቃድ ካላቀረቡ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ 30% ተቀናሽ እንደሚደረግባቸው ግልጽ ነው። በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ለአጭር ጊዜ በመምጣት በሰንጠረዥ 'ሐ" ሰር የሚወድቅ ገቢ ሊያገኙ ይችላሉ። የዚህ አይነት ሰዎች በኢትዮጵያ ነዋሪ ሆነው ሳለ በሕግ የተጣለባቸውን ግዴታ ቸል በማለት የመመዝገብ ግዴታቸውን ያልተወጡ ካልሆነ በስተቀር በኢትዮጵያ ነዋሪ ባለመሆናቸው የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር እና የንግድ ፈቃድ ሊሰጣቸው አይችልም። እነዚህ ድንጋጌዎች

በሕግ የተጣለባቸውን የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር እና የንግድ ፈቃድ የማውጣት ግዴታ ያልተወጠ ግብር ከፋዮችን እንጂ ግዴታዎቹ የሌሉባቸውን በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ እና በኢትዮጵያ ዘላቂ ድርጅት የሌላቸውን የሚመለከቱ አይደሉም።

1.7 ሌሎች ገቢዎች

በአዋጁ ሰንጠረዥ "ሀ"፣"ለ"፣"ሐ" እና "መ" ከተመለከቱት ውጪ ያሉት ሌሎች ገቢዎች 15% ግብር ሊከፈልባቸው እንደሚገባ የገቢ ግብር አዋጅ ይደነግጋል። ይህ የተደረገው በሠንጠረጉቹ ከተዘረዘሩት ውጪ ያሉ ገቢዎች ግብር ሳይከፈልባቸው እንዳይቀር ለማድረግ ነው።

ጥያቄ ሆኖ የቀረበው በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው በአዋጁ አንቀጽ 63 "ሌሎች ገቢዎች" በሚል የተመለከተውን ገቢ ያገኘ እንደሆነ ግብር ሊከፍል ይገባል ወይ? የሚለው ነው። የኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሥርዓት ነዋሪነትን የሚከተል ሲሆን ፤ በሕግ በተለዩ ገቢዎች ላይ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎች ጭምር ግብር እንዲከፍሉ የሚ ያደርግ ነው። የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 2 በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆኑ ሰዎችን በሚመለከት አዋጁ ተፈጻሚ የሚሆነው በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያገኙት ገቢ ላይ መሆኑን ይደነግጋል። በተጨማሪም የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 6(3) እና (4) በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው የንግድ ስራ ገቢ ኢትዮጵያ ውስጥ የተገኘ ነው የሚባለው የትኞቹን ገቢዎች ሲያገኝ እንደሆነ የሚዘረዝር ሲሆን "ሌሎች ገቢዎች" በዚህ ውስጥ አልተካተቱም። በሌላ በኩል በአዋጁ ክፍል 5 ከተዘረዘሩት የገቢ ዓይነቶች ውስጥ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ግብር የሚከፈልባቸው በስም በመለየት በግልጽ ተዘርዝረዋል። ስለሌሎች ገቢዎች የሚደነግገው አንቀጽ 63 በእነዚህ ገቢዎች ላይ በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ግብር ሊከፍል የሚገባ መሆኑን በግልጽ አይደነግግም። በመሆኑም ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብር ቀንሶ ስለማስቀረት የሚደነግገው አንቀጽ 89(1) ከዚህ አንጻር መተርጎም ይኖርበታል። በሌሎች ገቢዎች ላይ ሁሉ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ግብር ይከፍላል በባል ወደኢትዮጵያ ዕቃ የሚልኩ ሁሉ ግብር ሊቀነስባቸው ይገባል የሚል ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ስለሚሆን ከሕጉ ዓላማ እና መንፈስ ውጪ ነው።

1.8 ከኢትዮጵያ አየር መንገድ ጋር የተያያዙ የታክስ ጥያቄዎች

የኢትዮጵያ አየር መንገድ በየዓመቱ በሚያገኘው ትርፍ ላይ ሊከፍል የሚገባው ግብር የድርጅቱን ካፒታል ለማሳደግ እንዲውል በመንግሥት የተወሰነ በመሆኑ በዚህ ገቢ ላይ ግብር ባይጠየቅም፣ ከውጭ አገር ለሚያገኛቸው የቴክኒክ አገልግሎቶች ከሚፈፅማቸው ክፍያዎች እንዲሁም በብድር ላይ ከሚከፍለው ወለድ ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረግ አለበት የሚል ጥያቄ ይነሳል።

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከኢትዮጵያ ጋር ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት የሚያስችል ስምምነት በተፈራረመ ወይም ባልተፈራረመ አገሮች ከሚገኙ ድርጅቶች አገልግሎት የሚያገኝ ወይም በወሰደው ብድር ላይ ወለድ የሚከፍል መሆኑ ይታወቃል።

በመሠረቱ አየር መንገዱ ከውጭ አገር የሚያገኘው አገልግሎት ለሥራ አመራር ወይም ለቴክኒክ አገልግሎት በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የሚወድቅ እስከሆነ ድረስ በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 51(2) በተደተነገገው መሠረት ከሚፈፅመው ክፍያ ላይ 15% ግብር ቀንሶ ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት። ይሁን እንጂ አገልግሎቱ የተገኘው ከኢትዮጵያ ጋር ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት የሚያስችል ስምምነት በተፈራረመ አገር ከሚኖር ኩባንያ ከሆነ ታክሱ ከተከፋይ ሂሳብ ላይ መቀነስ አለበት ወይስ የለበትም የሚለው በስምምነቱ መሠረት የሚመራ ይሆናል። በአብዛኛው ስምምነት በቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ ላይ ታክሱ የሚሰበሰበው አገልግሎቱን የሰጠው ሰው ነዋሪ በሆነበት አገር ስለሆነ አፈፃፀሙ ስምምነቱን መከተል ይኖርበታል።

ከወለድ የሚገኝን ገቢ በተመለከተ ኢትዮጵያ በፈረመቻቸው ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት የሚያስችሉ ስምምነቶች በወለድ ገቢ ላይ የገቢው ምንጭ የሆነው አገር እና የገቢው ተጠቃሚ የሆነው ሰው ነዋሪ የሆነበት አገር ሁለቱም በተወሰነ መቶኛ ግብሩን መሰብሰብ ስለሚችሉ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በዚሁ መጠን ግብሩን ቀንሶ ማስቀረት ይኖርበታል። ወለዱ የሚከፈለው ተደራራቢ ግብርን ለማስቀረት የሚያስችል ስምምነት ባልተፈራረምንበት አገር ለሚኖር አበዳሪ ከሆነ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በወለዱ ገቢ ላይ 10% ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረግ አለበት።

1.9 <u>በካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ላይ ስለሚከፈል ግብር</u>

በአክሲዮን ዋጋ ዕድገት ጥቅም ላይ የሚከፈለው ግብር የሚሰላበት ዘዴ እንዲሁም የማይንቀሳቀስ ሃብት በሚተላለፍበት ጊዜ በዋጋ ዕድገት ጥቅም ላይ ግብር የሚሰላበት እና የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ የሚደረግበት አኳኋን ግልፅ ባለመሆኑ በአፈፃፀም ችግር ሲስተዋል ይታያል።

በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 59(3) ግብር የሚከፈልበትን ሀብት በማስተላለፍ የሚገኘው ጥቅም ሀብቱን በማስተላለፍ የተገኘው ዋጋ፤ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ ከነበረው ዋጋ በልጦ የተገኘው የገንዘብ መጠን መሆኑ ተመልክቷል። በመሆኑም ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ የነበረው ዋጋ እንዴት ይታወቃል? የሚለው በመጀመሪያ ምላሽ ማግኘት ያለበት ጥያቄ ይሆናል።

የዕቃዎች ዋጋ የገንዘብን የመግዛት አቅም መውደቅ ተከትሎ ሊጨምር እንደሚችል ይታወቃል። ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሰለዋጋ የሚደነግገው የሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ ማሻሻያ አንቀጽ 56(1) በአዋጁ የተመለከተው የምድብ "ሀ" እና 'ለ" ግብር የሚከፈልበት ሃብት ዋጋ የገንዘብ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ እንደሚደረግበት ይደነግጋል። የዋጋ ግሽበት ማስተካክያ የሚደረገው በፍጆታ ዕቃዎች ዋጋ ላይ ባለፈው ዓመት ያጋጠመውን አማካይ አመታዊ የዋጋ ግሽበት መሠረት በማድረግ ነው። በመሆኑም በአክሲዮን እና በማይንቀሳቀስ ሀብት ዋጋ ላይ በደንቡ በተደነገገው መሠረት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ይደረጋል።

በሂሳብ መዝገብ ላይ የሚሰፍረው የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ግብር የሚከፈልባቸው ሀብቶች ዋጋ ሀብቶቹ የተፈሩበት ዋጋ ነው። የዋጋ ግሽበት መኖሩ ቢታወቅም የእነዚህን ሀብቶች ዋጋ እንደገና በመተመን (revalue) የመዝገብ ዋጋቸውን ማሻሻል ሕግ አይፈቅድም። ይህም በመሆኑ እነዚህ ሀብቶች በሚተላላፉበት ጊዜ በመዝገብ ዋጋቸው እና በተላለፉበት ዋጋ መካከል ከፍተኛ ልዩነት በመኖሩ ግብር ከፋዮች ከፍተኛ የግብር ጫና ሰለሚያርፍባቸው የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ መደረጉ ተገቢ ነው።

በዚህም መሠረት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያው ሀብቱ ለተፈራበት ዋጋ እና ለሀብቱ ማሻሻያ ለወጣው ወጪ በሚከተለው ስሌት መሠረት ሊደረግ ይገባል።

ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ = ሀብቱ በተላለፈበት(በተሸጠበት) አመት የነበረው የዋጋ ግሽበት መቶኛ X ሀብቱ የተፈራበት ዋጋ

ሀብቱ በተገዛበት አመት የነበረው የዋጋ ግሽበት መቶኛ

ንብረቱን ለማሻሻል የወጣ ወጪ = ሀብቱ በተላለፈበት(በተሸጠበት) አመት የነበረው የዋጋ ግሽበት መቶኛ X የሀብቱ ማሻሻያ ወጪ

የሀብቱ ማሻሻያ በተረገበት አመት የነበረው የዋጋ ግሽበት

ከዚህ በኋላ ግብሩን ለማስላት የሚቀረው መረጃ ሀብቱ የተሸጠበት ዋጋ ይሆናል። በመሆኑም ሀብቱ የተሸጠበት ዋጋ አጠራጣሪ ከሆነ ገበያውን በመዳሰስ ግንኙነት በሌላቸው ሰዎች መካከል የተካሄደውን ግብይት ዋጋ በመነሻነት በመውሰድ የሸያጩን ዋጋ መወሰን ተገቢ ይሆናል። በዚህም መሠረት በሀብቱ ዋጋ እና በተሸጠበት ዋጋ ወይም ከማስተላፍ በተገኘው ጥቅም መካከል ያለው የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም በአዋጁ የተጣለው ግብር ይከፈልበታል።

አክሲዮንን በሚመለከት አክሲዮን በሁለት መንገድ ገበያ ላይ ሊውል እንደሚችል ይታወቃል። የመጀመሪያው ባለአክሲዮኖች አክሲዮናቸውን ሲሸጡ ሲሆን፣ ሁለተኛው ኩባንያው ራሱ ካፒታል ለማሳደግ አዳዲስ አክሲዮኖችን ለገበያ በሚያውልበት ጊዜ ነው።

ማናቸውም ኩባንያ የተለያየ ደረጃ ያላቸውን አክሲዮኖች የሚያወጣ ካልሆነ በስተቀር የኩባንያው አክሲዮኖች ዋጋ (par value) የተለያየ ሊሆን አይችልም። ሆኖም ኩባንያው አዲስ አክሲዮኖችን ለገበያ በሚያውልበት ጊዜ በንግድ ሕግ አንቀጽ 435 በተደነገገው መሠረት ከተሳፈላቸው ዋጋ (par value) በላይ እንዲሸጡ ሊያደርግ የሚችል ሲሆን፣ ይህም በተጨባጭ አክሲዮኖች የተሸጡበት የዋጋ ልዩነት ፕሪሚየም በሚል ይታወቃል። ኩባንያው በፕሪሚየም መልክ የሚያገኘው ገቢ በመጠባበቂያ ሂሳብነት ሊያዝ የሚችል ሲሆን፣ የዚህ የመጠባበቂያ ገንዘብ ተካፋዮች መሆን የሚችሉት አዲሶቹ አክሲዮኖች ከመሸጣቸው በፊት ባለአክሲዮን የነበሩት ሰዎች ብቻ መሆናቸውን አዲሱ የንግድ ሕግ አንቀጽ 435(2) ያመለክታል። በቀድሞው የንግድ ሕግ መሠረት ይህ ፕሪሚየም የሚከፋፈለው ለነባር እና ለአዲስ ባለአክሲዮኖች ነበር።

በሁለቱም ሁኔታዎች ኩባንያው አዲስ አክሲዮኖችን በመሸጥ ያገኘው ገቢ የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ግብር ሊከፈልበት የሚገባ ሲሆን፣ አከፋፈሉም በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 21 (4) እና የካፒታል ሀብቶችን በማስተላለፍ በሚገኘው ጥቅም ላይ ግብር ስለሚሰላበት ሁኔታ ከዚህ በላይ የተዘረዘረውን አሰራር የሚከተል ይሆናል።

ከማይንቀሳቀስ ሀብት (ሕንፃን ጨምሮ) በተገኘ የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ላይ ግብር በሚሰላበት ጊዜ ከላይ እንደተገለጸው የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ የሚደረግ ሲሆን፤ በገንዘብ ሚኒስቴር በተሳለፈው መመሪያ መሠረት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያው የሚደረገው የኢትዮጵያ ስታትስቲክስ ኤጀንሲ በየዓመቱ የሚያወጣውን አማካይ የዋጋ ግሽበት መረጃ መሠረት በማድረግ ይሆናል። በዚህም መሰረት ግብር ከፋዩ ሀንፃውን (የማይንቀሳቀሰውን ሀብት) በማስተላለፍ ካገኘው ገቢ ላይ ከዚህ በላይ በተገለጸው ስሌት መሰረት የሚደረስበት ሀብቱ በተላላፈበት ጊዜ የነበረው ዋጋ ተቀንሶ ባለው ልዩነት ላይ ግብር ሊከፈልበት ይገባል። የሚተላለፈው የንግድ ስራ ሃብት ከሆነ እና የማስተላለፉ ተግባር የሚፈፀመው በእንደገና መደራጀት ሂደት ውስጥ ከሆነ ግን በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 59 እና 35 እንዲሁም በዚህ ሰነድ ተራ ቁጥር 1.19 እንደተብራራው የሚከፈል የካፒታል ዋጋ እድገት ጥቅም ግብር አይኖርም።

ከኩባንያ እንደገና መደራጀት ውጪ የማይንቀሳቀስ ሃብት በማስተላለፍ የሚገኝ ጥቅም ደግሞ ለሁለት ይከፈላል። በገቢ ግብር ደንብ አንቀጽ 56(2) (ሀ) መሠረት ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ የነበረው ዋጋ (ለሀብቱ የተደረገ ወጪን ጨምሮ) እና በሀብቱ

የተጣራ የመዝገብ ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት በንግድ ስራው ገቢ ውስጥ ተካቶ የንግድ ትርፍ ግብር የሚከፈልበት ሲሆን፣ የንግድ ስራ ሀብቱ ከተላለፈበት ዋጋ ላይ ሀብቱ በተላለፈበት ጊዜ የነበረው ዋጋ (ለሀብቱ የተደረገ ወጪን ጨምሮ) ተቀንሶ የሚቀረው ሂሳብ በአዋጁ አንቀጽ 59 መሰረት የካፒታል ዋጋ እድገት ጥቅም ግብር የሚከፈልበት ይሆናል።

1.10 <u>የውጭ ምንዛሪ ጥቅም ወይም ኪሳራ</u>

በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 77(3) በውጭ ምንዛሪ ግብይት የተገኘ ጥቅም ወይም የደረሰ ኪሣራ ለግብር አከፋፈል ሲባል ግብይቱ በተከናወነበት የግብር ዓመት ውስጥ እንደተገኘ ጥቅም ወይም እንደደረሰ ኪሣራ ሆኖ መገለፅ እንደሚገባው ተመልክቷል።

ይህንን አንቀጽ በማስፈፀም ረገድ የሚታየው ክፍተት "የውጭ ምንዛሪ ግብይት" በሌለበት ሁኔታ ጥቅም ተገኝቷል ማለት ይቻላል ወይ? ግብይት ተፈፀመ የሚባለው መቼ ነው? ጥቅሙ የተገኘበት ወይም ኪሣራው የደረሰበት ጊዜ (in which they are realized) የሚባለው መቼ ነው? ከሚሉት ጋር የተያያዘ ነው።

በገቢ ግብር ደንብ አንቀጽ 44(6) "የውጭ ሃገር ገንዘብ ምንዛሪ ጥቅም" እና "የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሳራ" የሚሉት ሐረጎች በሚገባ ተተርጉመዋል። በደንቡ በተተረጎመው መሠረት "የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ጥቅም" ማለት ከውጭ ሃገር ገንዘብ ግብይት ጋር በተገናኘ በውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ተመን መዋዠቅ ምክንያት የተገኘ ጥቅም ነው። በመሆኑም ጥቅም ተገኝቷል ለማለት የውጭ ሃገር ገንዘብ ግብይት መኖር ያለበት ሲሆን፤ ሂሳቡ በብር ተለውጦ መመዝገቡ ብቻ ጥቅም ተገኝቷል አያሰኝም። "የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሳራ" ማለት ደግሞ ከውጭ አገር ገንዘብ ግብይት ጋር በተገናኘ በውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ተመን መዋዠቅ ምክንያት የሚደርስ ኪሳራ ነው።

በመሆኑም የውጭ ምንዛሪ ጥቅም ወይም ኪሣራ ደርሷል ለማለት የውጭ ምንዛሪ ግብይት ሊኖር ይገባል። የውጭ ምንዛሪ ግብይት በሌለበት ሁኔታ ጥቅም ወይም ኪሣራ አጋጥሟል ለማለት አይቻልም። በዚህ ረገድ የሚነሳው አንዱ አከራካሪ ጉዳይ ፕሮጀክቱ ከውጭ አገር በተገኘ ብድር ወይም ዕርዳታ የሚከናወን በሚሆንበት ጊዜ ሥራ ተቋራጩ ከብድሩ ወይም ከዕርዳታው ገንዘብ ላይ በውጭ አገር ባለ የባንክ ሂሳቡ በውጭ ምንዛሪ ገንዘብ ተቀብሎ ከውጭ አገር ለሚመጡ ዕቃዎች መግዣ ቢያውል ይህ ገንዘብ ወደ ብር ያልተለወጠ በመሆኑ የውጭ ምንዛሪ ጥቅም ወይም ኪሣራ ደርሷል ሊባል ይችላል ወይ? የሚለው ነው። በዚህ ዓይነቱ እንቅስቃሴ የምንዛሪ ግብይት (foreign currency exchange) ያልተካሄደ በመሆኑ ከውጭ ምንዛሪ ጥቅም ተገኝቷል ወይም ኪሣራ ደርሷል ሊባል አይገባም። ጥቅም ተገኝቷል

ወይም ኪሣራ ደርሷል የሚባለው ግብር ከፋዩ በውጭ ምንዛሪ ከተቀበለው ገንዘብ ውስጥ የተወሰነውን ወደአገር አስገብቶ ወደብር የለወጠ እንደሆነ ብቻ ነው። በመሆኑም በገቢዎች ሚኒስቴር የወጡ መመሪያዎች ከሕጉ ጋር እንዲጣጣሙ ሆነው የሚሻሻሉ ይሆናል።

በአገር ውስጥ የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ ያላቸው ሰዎች የውጭ ምንዛሪውን ወደባንክ ገቢ ካደረጉ በኋላ በየጊዜው በሚኖረው የምንዛሪ ለውጥ ምክንያት ወደባንክ ያስገቡት ገንዘብ ወደብር ቢለወጥ የሚኖረው ዋጋ ከፍተኛ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ የውጭ ምንዛሪው ግብይት የሚፈፀመው አስቀማጩ ገንዘቡን ወደብር ለውጦ ከባንኩ ለመውሰድ በሚጠይቅበት ጊዜ ነው። በመሆኑም ጥቅሙ የተገኘበት ወይም ኪሣራ የደረሰበት ቀን ሆኖ ሊወሰድ የሚገባው የውጭ ምንዛሪው ግብይት የተፈፀመበት ቀን እንጂ የውጭ ምንዛሪው ባንኩ ውስጥ ተቀምጦ ሳለ ቢመነዘር ኖሮ በሚል እሳቤ በብር የሚከፈለውን የገንዘብ መጠን ታሳቢ በማድረግ ሊሆን አይችልም። በሌላ በኩል አስቀማጩ በባንክ ሂሳቡ ያለውን የውጭ አገር ገንዘብ ወደውጭ አገር ቢልክ የተፈጸመ የውጭ ምንዛሪ ግብይት የሌለ በመሆኑ አስቀማጩ ባንክ በውጭ ምንዛሪ ግብይት ኪሳራ ደርሶበታል ሊባል አይችልም።

በሌላ በኩል ከውጭ ሃገር በኢትዮጵያ ንግድ መርከብ ተጭነው የሚመጡ ዕቃዎች የጭነት ዋጋ በኢትዮጵያ የባህር ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ አገልግሎት ድርጅት ስም በተከፈተ የውጭ ምንዛሪ የባንክ ሂሳብ ውስጥ ከተቀመጠ በኋላ በውጭ አገር በሚገኙ ባንኮች ወደሚገኘው የድርጅቱ የባንክ ሂሳብ ሲተላለፍ የውጭ ምንዛሪ ግብይት ኪሳራ ደርሷል በሚል የማካካሻ ጥያቄ ይቀርባል። ይህ ተግባር በአንድ ዓይነት የውጭ ምንዛሪ ተቀምጦ የነበረ ገንዘብ በዚያው የውጭ ምንዛሪ ወደውጭ አገር የሚላክበት በመሆኑ የተፈጸመ የውጭ ምንዛሪ ግብይት የለም። በመሆኑም በውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራ ደርሷል ሊባል አይችልም።

በተመሳሳይ አስመጪዎች ዕቃ ወደአገር ለማስገባት ሌተር ኦፍ ክሬዲት በከፈቱበት ቀን በነበረው የምንዛሪ ተመን እና ዕቃው ወደአገር በገባበት ጊዜ የጉምሩክ ኮሚሽን በዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ ለማስላት በሚጠቀምበት የዕለቱ የምንዛሪ ተመን መካከል ልዩነት ሊኖር ይችላል። ይሁን እንጂ የጉምሩክ ኮሚሽን ለቀረጥና ታክስ ስሌት ሲባል በጉምሩክ አዋጅ በተደነገገው መሠረት የዕለቱን የምንዛሪ ተመን መሠረት በማድረግ ስሌቱን የሚያከናውን ከሚሆን በስተቀር የተከናወነ የውጭ ምንዛሪ ግብይት የለም። በመሆኑም የውጭ ምንዛሪ ግብይት በሌለበት ሁኔታ የውጭ ምንዛሪ ጥቅም ተገኝቷል ወይም ኪሣራ ደርሷል ሊባል አይችልም።

በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ መመሪያ መሠረት ባንኮች ከስራ እንቅስቃሴያቸው ጋር በተያያዘ ከሚያገኙት የውጭ ምንዛሪ የተወሰነውን (አሁን ባለው መመሪያ 50%) ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገቢ እንዲያደርጉ ይገደዳሉ። አንዳንድ ባንኮች በዚህ

መመሪያ በተጣለብን ግዴታ ያጣነውን የውጭ ምንዛሪ ለመተካት ከተለያዩ ምንጮች ከፍ ባለ ዋጋ የውጭ ምንዛሪ በመግዛታችን ኪሳራ ያጋጠመን ስለሆነ ኪሳራው ሊካካስልን ይገባል የሚል ጥያቄ ያነሳሉ። በመጀመሪያ ደረጃ የዚህ አይነቱ ግብይትበሕጋዊ መንገድ የተፈጸመ መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል። ሕጋዊነቱ ከተረጋገጠ ጥያቄው የሚሆነው የዚህ ዓይነቱ ኪሳራ በገቢ ግብር ደንብ ለውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሳራ በተሰጠው ትርጉም ይሸፈናል ወይ? የሚለው ነው። ከዚህ በላይ እንደተመለከተው የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሳራ የሚባለው በምንዛሪ መዋዠቅ ምክንያት የደረሰ ኪሣራ ነው። የዚህ አይነቱ ባንኮች አጋጠመን የሚሉት ኪሣራ በውጭ ምንዛሪ መዋዠቅ ምክንያት የተፈጠረ ስላልሆነ በውጭ ምንዛሪ ግብይት ያጋጠመ ኪሣራ ነው ሊባል አይችልም።

አስመጪዎች በሌተር ኦፍ ክሬዲት መሠረት (value date) ክፍያ ፈጽመው ሰነዶችን ከተረከቡ በኋላ በውጭ ያሉ ባንኮች የውጭውን አገር ገንዘብ በወቅቱ ከባንኩ ሂሳብ ሳይወስዱ ይቆዩና ገንዘቡ ከባንኩ ሂሳብ ወጪ በሚደረግበት እለት በነበረው የምንዛሪው ተመን ከፍ ማለት ምክንያት ባንኩ የውጭ ምንዛሪ ግብይት ኪሣራ ሊያጋጥመው ይችላል። የዚህ አይነቱ ኪሣራ ከላይ በተጠቀሰው የገቢ ገብር ደንብ አንቀጽ 44 በተመለከተው መሰረት በውጭ ምንዛሪ ግብይት የደረሰ በመሆኑ ሊካካስ ይገባል።

በአጠቃላይ በውጭ ምንዛሪ ግብይት ኪሣራ አጋጥሟል ወይም ጥቅም ተገኝቷል የሚባው በገቢ ግብር አዋጅ እና ደንብ የተደነገገው ሲሟላ ብቻ ሲሆን፤ ግብር ከፋዩ ገቢውን ለማግኘት የሚያደርጋቸው ወጪዎች ካሉ በሕግ የተዘረጋውን ሥርዓት ጠብቀው ተቀናሽ ሊደረጉ ይገባል።

1.11 <u>በረዥም ጊዜ ውል በተገኘ ገቢ ላይ የሚከፈለው ግብር አወሳሰን</u>

ለረዥም ጊዜ በሚቆይ ውል በተገኘ ገቢ ላይ ግብር የሚሰላበት ሁኔታ ውስብስብ ያለ አሰራርን የሚከተል በመሆኑ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ሊወጣለት የሚገባ ቢሆንም በተደጋጋሚ በሚነሱ የተወሰኑ ጥያቄዎች ላይ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ይሆናል።

በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 32 ስለረዥም ጊዜ ውሎች ግብር አከፋፈል ከተደነገገው ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ የሚነሱ ሁለት ጥያቄዎች ያሉ ሲሆን፣ የመጀመሪያው ግብሩ "በግብሩ ዓመቱ የተጠናቀቀውን መቶኛ መሠረት በማድረግ" እንደሚሰላ በተመለከተው መሠረት የተጠናቀቀው ሥራ በምን ይረጋገጣል? የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው የሪል ስቴት የረዥም ጊዜ ውል ይባላል ወይ? የሚል ነው።

በተጠቀሰው አንቀጽ እንደተተረጐመው ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ውል ማለት ሥራው ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በ12 ወራት ውስጥ ይጠናቀቃል ተብሎ ከሚገመተው በስተቀር በተጀመረበት የግብር ዓመት ውስጥ ያልተጠናቀቀ የማምረት፣ የመትከል ወይም የግንባታ ሥራ እንዲሁም ከእነዚህ ጋር የተያያዘ አገልግሎት ነው። በመሆኑም ለረዥም ጊዜ የሚቆይ ውል የሚባለው በውል ሰጪው እና በውል ተቀባዩ መካከል የተፈፀመ አንድ ዕቃ ለማምረት፣ የተከላ ሥራ ለመሥራት ወይም የግንባታ ሥራ ለማከናወን የተፈፀመ እና ከ12 ወራት በላይ የሚፈጅ ውል ነው። የሪል እስቴት ወይም ቤት ሠርቶ የመሸጥ ውል የረዥም ጊዜ ውል ይባላል ወይ? የሚለው በበርካታ አገሮች የተለያየ ትርጉም ሲሰጠው ይታያል። የሪል እስቴት አልሚዎች ለገበያ የሚያቀርቡትን ቤት በሁለት መንገድ ለገበያ ሲያቀርቡ ይታያል። አንዳንዶቹ ቤቱን በራሳቸው ወጪ ገንብተው ለገበያ የሚያቀርቡ ሲሆን፣ የተቀሩት ደግሞ ከቤቱ ገዥ የቅድሚያ ክፍያ በመቀበል ቤቱን በመገንባት ለገዥው ያስረክባሉ።

የሪል እስቴት አልሚዎች የቤቱን ግንባታ ወጪ ከራሳቸው የገንዘብ ምንጭ ወይም ከባንክ በሚያገኙት ብድር በመሸፈን ቤቱን ለገበያ የሚያቀርቡ በሚሆንበት ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ሽያጭ እንደማናቸውም ዕቃዎችን አምርቶ ለገበያ እንደሚያቀርብ ግብር ከፋይ መቆጠር ያለበት ሲሆን፣ የረዥም ጊዜ ውል ለሚለው ሐረግ በአዋጁ በተሰጠው ትርጉም ሥር የሚወድቅ ሊሆን አይችልም። ይሁን እንጂ የሪል እስቴት አልሚው ከደንበኞች ጋር በሚያደርገው ውል መሠረት ከደንበኞቹ የቅድሚያ ክፍያ ወይም በየጊዜው የሚፈፀም ክፍያ (installment payment) በመቀበል ቤቶችን ገንብቶ ለደንበኛው የሚያስረክብ ከሆነ የዚህ ዓይነቱ ውል በአዋጁ ለረዥም ጊዜ ውል በተሰጠው ትርጉም ሥር ስለሚወድቅ ገቢውን ማስታወቅ እና ግብሩን መክፈል ያለበት ስለረዥም ጊዜ ውሎች የተደነገገውን በመከተል መሆን አለበት።

በመደበኛ ሁኔታ በግንባታ ሥራ ውል መሠረት የተጠናቀቀው ሥራ የሚረጋገጠው የግንባታውን ሥራ የሚከታተለው ተቆጣጣሪ መሀንዲስ በሚሰጠው የተጠናቀቀውን ሥራ መጠን በሚያሳየው የክፍያ የምስክር ወረቀት ነው። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ የተጠናቀቀው ሥራ ሙሉ በሙሉ ተለክቶ የምስክር ወረቀት ስለማይቀርብበት የተጠናቀቀው ሥራ በምስክር ወረቀቱ ከተመለከተው የሥራ መጠን ሊበልጥ ይችላል። በመሆኑም የተጠናቀቀው ሥራ ሙሉ በሙሉ ተለክቶ በምስክር ወረቀቱ ውስጥ የተካተተ ከሆነ በምስክር ወረቀቱ ላይ የተመለከተው የተጠናቀቀው ሥራ መቶኛ ሆኖ ሊወሰድ የሚገባ ሲሆን፣ ከተጠናቀቀው ሥራ ውስጥ በመሀንዲስ ተለክቶ በምስክር ወረቀት ውስጥ ያልተካተተ ካለ ግን በምስክር ወረቀቱ ያልተካተተው የተጠናቀቀ ሥራ ጭምር ከግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል።

በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ ግብር ከፋዩ የተቀበለው ሥራው የሚገኝበትን ደረጃ መሠረት በማድረግ የሚፈፀም ክፍያ (Progress payment) እና የመጨረሻ ክፍያ (final payment) በግብር ስሌት ውስጥ መካተት አለበት። በተጨማሪም በገቢ ግብር

አዋጅ የተፈቀደ እስከሆነ ድረስ ግብር ከፋዩ ያወጣውን ወጪ እንዲሁም ያጋጠመውን ኪሣራ በግብር ስሌት ውስጥ ማካተት ይኖርበታል።

ለረዥም ጊዜ የግንባታ ውል የግብር ስሌት መሠረት የሚሆነው በግብር ዓመቱ ውስጥ ሥራው የሚገኝበትን ደረጃ ተከትሎ የተፈፀመ ክፍያ እና የመጨረሻው ክፍያ ብቻ ሳይሆን በውሉ መሠረት የተደረገ የዋጋ ማሻሻያ (price escalation); ተጨማሪ ስራ (variation) ወይም በስራ ተቋራጩ የቀረበ በአሠሪው ወይም አማባብ ባለው አካል የተረጋገጠ የይገባኛል ጥያቄን (claim) ጨምሮ በግብር ዓመቱ ለተጠናቀቀው ሥራ አስሪው ሊከፍል የሚገባው ሂሳብ ጭምር ነው።

ግብር ከፋዩ በውሉ መሠረት በግብር ዓመቱ ሊጠይቅ የሚገባውን ማናቸውንም ክፍያ ሳይጠይቅ በማዘግየት የክፍያውን ጊዜ ማስተላለፍ እንዲሁም በውሉ መሠረት ክፍያውን ሊያረጋግጥ የሚገባው አካል ክፍያውን ሳያረጋግጥ እንዲዘገይ ማድረግ አይችልም።

ለማጠቃለል ከዚህ በላይ እንደተገለጸው የተጠናቀቀውን ሥራ መቶኛ መሠረት በማድረግ ገቢው በንግድ ሥራ ገቢ ውስጥ ሊካተት የሚገባ ሲሆን፣ ግብር ከፋዩ በዓመቱ ያወጣው ወጪ ከአጠቃላይ የውሉ ወጪ ግምት ጋር እንዲነፃፀር በማድረግ በወጪነት ሊያዝ ይገባል።

1.12 <u>ለተቀጣሪ ከገበያ ወለድ በታች ብድር በመስጠት የሚገኝ ጥቅም</u>

ከመቀጠር በዓይነት የሚገኝ ጥቅም ስለሚሰላበት ሁኔታ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ የተደነገገ ቢሆንም ድንጋጌዎቹ ግልፅ ባለመሆናቸው በአፈፃፀም ከፍተኛ ችግር የሚያጋጥም ሲሆን፣ ወጥነት ያለው አፈፃፀም አይታይም።

በዚህ ረገድ የአፈጻጸም ችግር ከሚታይባቸው ጥቅሞች አንዱ ተቀጣሪ በሚወስደው ብድር ላይ ከገበያ በታች የሆነ ወለድ መክፈል ነው። ይህንን ጥቅም ለማስላት አንዳንዶች በአጠቃላይ በባንክ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያለውን የወለድ መጣኔ የሚጠቀሙ ሲሆን፣ የተቀሩት ተቀጣሪው በሚሠራበት ባንክ ውስጥ ለደንበኞች ብድር በሚሰጥበት ወለድ እና ተቀጣሪው ብድሩን ባገኘበት ወለድ መካከል ያለውን ልዩነት የሠራተኛው ጥቅም እንደሆነ አድርገው ግብሩን ያሰላሉ።

ባንኮች ለተለያየ የንግድ ሥራ ወይም የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ እንዲሁም ለግል ዓላማ በሚውል ብድር ላይ ወለድ የሚያስከፍሉበት የተለያየ የብድር መጣኔ አላቸው። በመሆኑም ከባንኩ ጋር ግንኙነት ለሌላቸው ተበዳሪዎች ብድር በሚሰጡበት ጊዜ ተፈጻሚ በሚሆነው ለእያንዳንዱ ዘርፍ በተወሰነው ወለድ እና ሠራተኛው ለዚሁ ዘርፍ ብድር በሚወስድበት ጊዜ የሚያስከፍሉት ወለድ ያነሰ ከሆነ ልዩነቱ ሠራተኛው

ያገኘው ጥቅም እንደሆነ ተደርጐ መውሰዱ ተገቢ ይሆናል። ከዚህ ውጪ ሠራተኛው የማይሠራባቸው ባንኮች ተበዳሪዎቻቸውን የሚያስከፍሉት ወለድ በተለያየ ምክንያት ከፍ ወይም ዝቅ ሊል ስለሚችል ይህንን እንደማነፃፀሪያ መውሰድ ፍትሀዊ ካለመሆኑም በላይ የሠራተኛውን ወይም የመንግሥትን ጥቅም የሚጐዳ ሊሆን ይችላል።

1.13 <u>ከአርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች ለሚፈፀም ግዥ የሚቀርብ የወጪ ማስረጃ</u>

በግብርና ንግድ ሥራ ላይ ከተሠማሩት በስተቀር ግለሰብ አርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች የንግድ ሥራ ፈቃድ እንዲያወጡ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ታክስ እንዲሰበስቡ በሕግ ግዴታ አልተጣለባቸውም። በዚህም ምክንያት ከእነዚህ አርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች ግዥ የሚፈፅሙ ግብር ከፋዮች ሕጋዊ ደረሰኝ ማቅረብ ስለማይችሉ በወጪው አያያዝ ረገድ ከፍተኛ ያለመግባባት ይነሳል።

ከእነዚህ አርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች በቀጥታ የሚፈፀም ግዥ መጠኑ ከፍተኛ ሊሆን አይችልም። በመሆኑም መጠኑ አነስተኛ እስከሆነ ድረስ አከራካሪ የሚሆነው ዋጋው ይሆናል።

በመሆኑም ኩባንያዎች ከአርሶ አደሮች/አርብቶ አደሮች ግዥ በሚፈፅሙበት ጊዜ ሻጩ በትክክል አርሶ አደር/አርብቶ አደር መሆኑን ለማረጋገጥ የመታወቂያውን ወይም የመሬት ይዞታ የምስክር ወረቀት ፎቶ ኮፒ በማያያዝ የአርሶ አደሩን/አርብቶ አደሩን ስምና አድርሻ በክፍያ ሰነድ (Payment voucher) ላይ በመጻፍ ተቀባዩን አስፈርመው ማቅረብ ይኖርባቸዋል። በዚህ ዓይነቱ ሰነድ የተመለከተው ግዥ የተፈፀመበት ዋጋ ከሌሎች ተመሳሳይ ግብይቶች ዋጋ ጋር ተቀራራቢ ከሆነ ወጪው በተቀናሽነት ሊያዝ ይገባል።

ግብር ከፋዩ ከአርሶአደር/ አርብቶ አደር ለፈጸመው ግዢ ማሰረጃ ማቅረብ ካልቻለ የታክሱ ባለስልጣን የግብይቱን ትክክለኛ የገበያ ዋጋ በግምት ሊወስን ይችላል። ይሁን እንጂ ግብር ከፋዩ ማስረጃ ባለማቅረቡ መንግስት ከሻጩ ሊያገኝ ይችል የነበረውን ገቢ በማሳጣቱ የዚህ አይነቱን ድርጊት ለማስቆም በገቢዎች ሚኒስቴር በወጣው መመሪያ መሰረት የተገመተውን ወጪ 65% ብቻ በወጪነት በመያዝ ቀሪውን ውድቅ ማድረግ ይቻላል።

1.14 <u>የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት ግብር አከፋፈል</u>

የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት ከሚያገኘው ትርፍ ውስጥ የተወሰነውን ወደነዳጅ ማረጋጊያ ፈንድ ገቢ የሚያደርግ በመሆኑ ሊከፍል የሚገባው ግብር ሊሰላ የሚገባው ወደነዳጅ ማረጋጊያ ፈንድ ገቢ የሆነው ገንዘብ ተቀንሶ በሚቀረው ሂሳብ ላይ ነው ወይስ ወደነዳጅ ማረጋጊያ ፈንድ ገቢ የሚሆነው ሂሳብ ከመቀነሱ በፊት ባለው ትርፍ ላይ ነው? የሚል ጥያቄ ይነሳል።

የነዳጅ ማረጋጊያ ፈንድ ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 247/2001 (እንደተሻሻለ) አንቀጽ 5 የኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት የአገር ውስጥ የነዳጅ መሸጫ ዋጋ በሚወሰንበት ጊዜ ለነዳጅ መግዣና ለሌሎችም ጉዳዮች ታሳቢ ተደርገው በነበሩ ወጪዎች እና በትክክል በተደረገው ወጪ መካከል የሚኖረውን ልዩነት ለነዳጅ ማረጋጊያ ፈንድ ገቢ ማድረግ እንደሚገባው ይደነግጋል።

በዚህ የአዋጁ ድንጋጌ መሠረት የኢትዮጵያ ነዳጅ ደርጅት ለነዳጅ ግዥ ያወጣው ወጪ የአገር ውስጥ የነዳጅ መሸጫ ዋጋ በሚወሰንበት ጊዜ ታሳቢ ተደርጐ ከነበረው የነዳጅ መግዣ ዋጋ በታች ከሆነ ልዩነቱን ለነዳጅ ማረጋጊያ ፈንድ ገቢ ማድረግ ይኖርበታል።

የተጠቀሰው ድንጋጌ እንደሚያዘው ወደነዳጅ ማረጋጊያ ፈንድ ገቢ የሚደረገው ነዳጅ በትክክል በተገዛበት ወጪ እና የነዳጅ በሚወሰንበት ጊዜ በተገመተው የነዳጅ ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት እንጂ ከትርፉ ላይ ሊሆን አይገባም። ወደነዳጅ ማረጋጊያ ፈንድ ገቢ የሚደረገው ሂሳብ የአዋጅ/የሕግ ግዴታ ስለሆነ ይህ ሂሳብ ለኢትዮጵያ ነዳጅ ድርጅት በወጪነት መያዝ ይኖርበታል።

1.15 <u>በክፍያ ስምምነት ውስጥ እና በአቤቱታ ላይ ያሉ ታክስ ከፋዮች የባንክ ዋስትና ጥያቄ</u>

የክፍያ ስምምነት ፈርመው የግብር እና የታክስ ግዴታቸውን በመወጣት ላይ የሚገኙ እንዲሁም የግብር ውሳኔ ማስታወቂያ ደርሷቸው በሕግ አግባብ በአቤቱታ ላይ የሚገኙ ግብር ከፋዮች የባንክ ክሊራንስ ለማግኘት የባንክ ዋስትና አንዲያቀርቡ መጠየቁ ፍትሃዊ አይደለም የሚል ቅሬታ ይነሳል።

የባንክ ዋስትና ለማግኘት ግብር ከፋዩ የዋስትናውን ገንዘብ መጠን ያህል ማስያዝ ወይም ንብረት በዋስትና ማቅረብ ስላለበት የባንክ ዋስትና መጠየቅ ግብር ከፋዮች ተበድረው የንግድ ስራ እንቅስቃሴያቸውን ለማስፋፋት ለሚያደርጉት ጥረት እንቅፋት ሊሆን ይችላል። በሌላ በኩል ባንኩ የግብር ከፋዩን ንብረት በመያዣነት ተቀብሎ ብድር መስማማቱን የግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ከገለጸ ባንኩ የሚሰጠው ብድር

ባይከፈል በንብረቱ ላይ የቀደምትነት መብት ስለሚኖረው የግብር እዳውን ለመሰብሰብ የማይቻልበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። በመሆኑም እነዚህን ሁለት የጥቅም ግጭቶች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መፍታት ያስፈልጋል።

በዚህም መሰረት ግብር ከፋዩ የሚፈለግበትን ግብር 50% ወይም ከዚያ በላይ በማስያዝ በግብር ይግባኝ ወይም በፍርድ ቤት በክርክር ላይ የሚገኝ ከሆነ የባንክ ዋስትና ሳይጠየቅ የባንክ ክሊራንስ እንዲሰጠው ማድረግ ተገቢ ይሆናል፡ ግብር ከፋዩ

የክፍያ ስምምነት ላይ ወይም በአቤቱታ አጣሪ የስራ ክፍል ጉዳዩ በመታየት ላይ የሚገኝ ከሆነ ግን የባንክ ክሊራንስ ከመሰጠቱ በፊት የባንክ ዋስትና ወይም ግብር ከፋዩ ከእዳ ነጻ የሆነ ሃብትና ንብረት ያለው መሆኑን የሚያስረዳ ማስረጃ ካቀረበ እና ይህ ንብረት እንዳይሸጥ እንዳይለወጥ ለማድረግ ፈቃደኛ መሆኑን በጽሁፍ ካረጋገጠ ንብረቱን በዋስትና በመያዝ የባንክ ክሊራንስ እንዲሰጠው ማድረግ የተሻለ ይሆናል።

በመሆኑም የገቢዎች ሚኒስቴር ያወጣው መመሪያ እነዚህን ከግምት ውስጥ ባስገባ ሁኔታ እንዲሻሻል ማድረግ ተገቢ ነው፡

1.16 <u>ከፍተኛ የአዲት ስጋት ያለባቸው የሚጠየቁት የባንክ ዋስትና</u>

በአዲት ስጋት መስፈርት መሠረት ከፍተኛ የአዲት ስጋት የሚታይባቸው ግብር ከፋዮች በክፍያ ስምምነት መሠረት ግዴታቸውን ለመወጣት የባንክ ዋስትና እንዲያቀርቡ መጠየቅ ጫናን አሳድሯል የሚል ቅሬታ ይነሳል።

የዚህ አይነት ግብር ከፋዮች ከፍተኛ የአዲት ስጋት የሚታይባቸው ቢሆንም አዲቱ ያልተከናወነ በመሆኑ ግብር የሚፈለግባቸው መሆን ያለመሆኑ አይታወቅም። ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ከላይ እንደተገለጸው ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቀውን የባንክ ዋስትና እንዲያቀርቡ መጠየቅ አግባብ አይሆንም።

በዚህም መሠረት ግብር ከፋዩ የባንክ ዋስትና ማቅረብ ሳይጠየቅ የባንክ ክሊራንስ እንዲያገኝ በሚያስችል አኳኋን መመሪያው ሊሻሻል ይገባል።

1.17 <u>ግብር ከፋዩ ባስታወቀው ገቢ ላይ ማሻሻያ ለማድረግ የሚያቀርበው ጥያቄ</u>

በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሠረት ግብር ከፋዩ በራሱ በተዘጋጀው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ላይ ማስተካከያ ለማድረግ ጥያቄ ሲያቀርብ በአዲት ስጋት መስፈርት መሠረት ከፍተኛ የአዲት ስጋት የሚታይበት ነው በሚል ምክንያት ጥያቄው ውድቅ መደረጉ ከሕጉ ጋር የማይጣጣም ነው የሚል ቅሬታ ይቀርባል።

የታክስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 29 የራሱን የታክስ ስሌት ያዘጋጀ ታክስ ከፋይ ያቀረበውን በራስ የተዘጋጀ የታክስ ሰሌት ማስታወቂያ ባለሥልጣኑ እንዲያሻሽልለት ሊያመለክት እንደሚችል እና ባለሥልጣኑም በ120 ቀናት ውስጥ ስሌቱ እንዲሻሻል መወሰን ወይም ማመልከቻውን ውድቅ ማድረግ እንደሚችል ይደነግጋል። ከዚህ የአዋጁ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው ባለሥልጣኑ ማመልከቻውን ውድቅ ሊያደርግ የሚችለው በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2(ሀ) መሠረት የቀረበው የማሻሻያው ምክንያት በቂ ሳይሆን ሲቀር ነው። ከዚህ ውጪ በሆነ ምክንያት መብቱን መንፈግ ከሕጉ ጋር የሚጣጣም አይደለም።

በመሆኑም ማመልከቻው ውድቅ መደረግ ያለበት በሕጉ በተገለፀው መሠረት የቀረበው ምክንያት አሳማኝ ሆኖ በማይገኝበት ጊዜ ብቻ መሆን አለበት።

1.18 <u>ባንኮች የሚይዙት የኪሣራ መጠባበቂያ ሒሳብ</u>

የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 33 የፋይናንስ ተቋማት የሚይዙት የመጠባበቂያ ሂሳብ ተቀናሽ የሚደረግበት አኳኋን የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ እንደሚወሰን ይደነግጋል። ይህንን የአዋጁን ድንጋጌ መሠረት በማድረግ የወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ አንቀጽ 45 ማንኛውም ባንክ በአንድ የግብር ዓመት ለኪሳራ የያዘው የመጠባበቂያ ሂሳብ በኢትዮጵያ ብሄራዊ ባንክ ባንክ በተቀመጠ የጥንቃቄ መስፈርት መሠረት እስከተሰላ እና ከፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች ጋር የተጣጣመ እስከሆነ ድረስ በግብር አመቱ የመጠባበቂያ ሒሳብ መጠኑ 80% በተቀናሽ ወጪ እንደሚያዝለት ይደነግጋል።

በእነዚህ አንቀጾች አፈጻጸም ረገድ አከራካሪ የሆኑት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በተቀመጠ የጥንቃቄ መስፈርት መሠረት እና በፋይናንስ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መካከል ልዩነት ያለ እንደሆነ ተፈጻሚ የሚሆነው የትኛው ነው? በመጠባበቂያነት የሚያዘው ከብድር ጋር ለተያያዘው ብቻ ነው ወይ? የሚሉት ናቸው።

ከደንቡ ድንጋጌ መረዳት እንደሚቻለው ሁለቱ መስፈርቶች "እና" በሚል የተያያዙ ናቸው። በመሆኑም ሁለቱም ተደጋግፈው ስራ ላይ ሊውሉ ይገባል ። በመሆኑም የመጠባበቂያው ስሌት መከናወን ያለበት ብሄራዊ ባንክ ባወጣው የጥንቃቄ መስፈርት (የመጠባበቂያ ሂሳብ ዓይነት እና መጠን መሰረት) ሲሆን፤ የሂሳብ አመዘጋገቡ የሂሳብ ሪፓርት አቀራረብ ደረጃዎችን መከተል ይኖርበታል። በመሆኑም የመጠባበቂያው ሂሳብ ዓይነት እና የመጠባበቂያው መጠን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ ቁጥር SD/969/2018 ከተወሰነው የተለየ ሊሆን አይችልም።

ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ባወጣው መመሪያ "ሌሎች ሀብቶች" የሚለው ያልተተረጎመ በመሆኑ ይህንን ድንጋጌ ያለአግባብ የመጠቀም አዝማሚያ ይታያል፡ የደንቡ አንቀጽ 45 የመጠባበቂያው ዓይነት በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚወሰን መሆኑን ስለሚደነግግ ወደፊት ከባንኩ ጋር ውይይት በማድረግ ማስተካከያ እንዲደረግ ከሚጠየቅ በስተቀር ባንኩ ባወጣው መመሪያ የተፈቀደውን መጠባበቂያ መከልከል የሚቻልበት የሕግ አግባብ አይኖርም፡፡

1.19 <u>የአንድን ድርጅት ሀብት በዓይነት መዋጮነት በማስተላለፍ የሌላ ድርጅት ባለአክሲዮን መሆን</u>

ድርጅቶች ያላቸውን ሀብት በዓይነት መዋጮነት በማዋጣት የሌላ ድርጅት ባለአክሲዮን ሲሆኑ በዓይነት መዋጮነት የተላለፈው ሀንጻ ከካፒታል ዋጋ እድገት በሚገኝ ጥቅም ላይ የሚከፈለው ግብር ሊከፈልበት የሚገባ ስለመሆን ያለመሆኑ ክርክር ይነሳል፡፡

የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 59 (6) የተላለፈው የንግድ ስራ ሀብት በሚሆንበት ጊዜ የአዋጁ አንቀጽ 35 ተፈጻሚ እንደሚሆን ይደነግጋል፡፡ ሰለኩባንያ እንደገና መደራጀት የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 35 ደግሞ ለእንደገና መደራጀት የተሰጠውን ትርጉም በሚያሟላ አካኋን አንድ ኩባንያ የንግድ ስራ ሀብቱን ያስተላለፈ እንደሆነ የንግድ ስራ ሀብቱን እንደ መሸጥ፤ መለወጥ ወይም መስጠት ተደርጎ እንደማይወሰድ እንዲሁም ሀብቱ የተላለፈለት ሰው በተላለፈለት ሀብት ለውጥ አክሲዮን የሰጠ እንደሆነ ለአክሲዮኖች የተደረገው ወጪ የተላለፈው ሀብት ማስተላለፍ በሚከናወንበት ጊዜ ከነበረው ዋጋ ጋር እኩል መሆን እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ በመሆኑም የንግድ ስራ ሃብት የማስተላለፉ ተግባር የተከናወነው በእንደገና መደራጀት ሂደት ከሆነ የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም እና የሚከፈል ግብር አይኖርም፡፡ የተላለፈው ከንግድ ስራ ሃብት ውጪ ከሆነ ግን አንቀጹ "በማስተላለፍ" እና "ጥቅም" የሚሉትን ቃላት የሚጠቀም በመሆኑ ከእንደገና መደራጀት ውጪ ሀብት ለሌላ ሰው ሲተላለፍ የተገኘ ጥቅም ግብር ይከፈልበታል፡፡

በመሆኑም ለምሳሌ ከእንደገና መደረጀት ውጪ በዓይነት መዋጮነት የተላለፈው ሕንፃ ቢሆን እና ህንጻው የተላለፈው ከተፈራበት ዋጋ በላይ ከሆነ አስተላላፊው የካፒታል ዋጋ እድገት ጥቅም ያገኘ ስለሆነ በአዋጁ በተደነገገው መሰረት የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ግብር ሊከፍል ይገባል፡፡

1.20 <u>ኪሣራን ስለማሸጋገር</u>

በገቢ ግብር አዋጅ 979/2008 አንቀጽ 26 መሰረት ኪሳራ የሚሸጋገረው ትርፍ የሚገኝበት የግብር ዘመን እየተመረጠ ነው ወይስ የአምስቱ ዓመት ጊዜ የሚቆጠረው በተከታታይ ነው? የሚል ጥያቄ ይነሳል፡፡ የዚህ ጥያቄ ዋናው መነሻ ሳይካካስ የሚቀር ኪሳራ ሊኖር አይገባም የሚል ነው፡፡

የአንቀጽ 26 ንዑስ አንቀጽ 2 ግብር ከፋዩ በግብር አመቱ ኪሳራ ካጋጠመው በግብር ዓመቱ የደረሰውን ኪሣራ ለሚቀጥለው የግብር ዓመት ለማሸጋገር እንደሚችል ከሚደነግግ በስተቀር ግብር የሚከፈልበት ገቢ ወደሚገኝበት አመት አይልም። ከዚህም በተጨማሪ የዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ግብር ከፋዩ የደረሰበትን ኪሣራ ኪሣራው ከተከሰተበት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ ከሚቆጠሩ አምስት የግብር ዓመታት በላይ ማሸጋገር እንደማይችል ይደነግጋል።

በመሆኑም ኪሳራው ካጋጠመ ጊዜ ጀምሮ በአምስት ተከታታይ ዓመታት ውስጥ ሊካካስ ካልቻለ የሚካካስበት የሕግ አግባብ የለም።ጤናማ በሆነ የንግድ አሰራር ውስጥ አንድ የንግድ ስራ በተከታታይ እየከሰረ ሊቀጥል ስለማይችል ሕጉ የጊዜ ገደብ ያስቀመጠው ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው። ሆኖም በማምረት ተግባር ላይ የተሰማራ ግብር ከፋይ ሶስተኛ ኪሳራ ካጋጠመው እና ይህ ኪሣራ በትክክል ያጋጠመ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ካቀረበ በተሻሻለው የገቢ ግብር ደንብ መሠረት የገንዘብ ሚኒስቴር ሦስተኛው ኪሣራ ጭምር እንዲካካስ ሊፈቅድ ይችላል።

ከኪሣራ ማሸጋገር ጋር በተያያዘ የሚነሳው ሌላው ጥያቄ አንድ ግብር ከፋይ በኢንቨስትመንት ማበረታቻ ደንብ፤ በገቢ ግብር ደንብ እና በሌሎች የመንግሥት ውሳኔዎች መሠረት የሚካካስ ኪሣራ ቢኖረው የትኛው ቀድሞ ይካካሳል? የሚል ነው። በገቢ ግብር ደንብ ማሻሻያ አንቀጽ 42(1) በመጀመሪያ ያጋጠመ ኪሣራ ቀድሞ የሚካካስ መሆኑ የተመለከተ በመሆኑ ኪሳራው ያጋጠመበትን ጊዜ ተከትሎ በቅደም ተከተል ማካካሻው የሚደረግ ይሆናል።

1.21 <u>ባንኮች በሌላ ባንክ ገንዘብ በማስቀመጥ የሚያገኙት ወለድ ግብር አከፋፈል</u>

ባንኮች ለሌሎች ተበዳሪዎች በማበደር ያገኙት የወለድ ገቢ ላይ 30 ከመቶ ግብር የሚከፍሉ ሆኖ ሳለ አንደኛው ባንክ በሌላኛው ባንክ ገንዘብ በማስቀመጥ በሚያገኘው የወለድ ገቢ ላይ 5% መክፈሉ ተገቢ አይደለም የሚል ጥያቄ ይነሳል።

የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 56 በፋይናንስ ተቋማት ገንዘብ አስቀምጦ የወለድ ገቢ የሚያገኝ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው በወለድ ገቢው ላይ 5% ግብር ሊከፍል እንደሚገባ፤ በሌላ ማናቸውም ሁኔታ (ለምሳሌ ከፋይናንስ ተቋማት ውጭ) የሚያገኘው ወለድ 10% ግብር እንደሚከፈለት ይደነግጋል። በመሆኑም ባንኮችን ጨምሮ ማናቸውም የኢትዮጵያ ነዋሪ በፋይናንስ ተቋማት በሚኖረው ተቀማጭ ገንዘብ ላይ በሚያገኘው ወለድ ሊከፍል የሚገባው ግብር 5% ነው። ይህ ግብር ማናቸውም ወጪ ተቀናሽ ሳይደረግ በጠቅላላው የወለድ ገቢ ላይ የሚከፈል በመሆኑ በጣም ዝቅተኛ ነው ሊባል አይችልም። ሕጉ ልዩነት ሳያደርግ ማናቸውም የኢትዮጵያ

ነዋሪ በተቀማጭ ገንዘብ ላይ በሚያገኘው ወለድ ሊከፍል የሚገባው ግብር 5% መሆኑን የሚደነግግ ስለሆነ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ ባንኮች በተቀማጭ ገንዘብ ላይ በሚያገኙት ወለድ ላይ ከዚህ ውጪ እንዲከፍሉ ማድረግ አይቻልም።

በሌላ በኩል በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ ባንኮች ከኢትዮጵያ ውጪ ባሉ የፋይናንስ ተቋማት ገንዘብ በማስቀመጥ የሚያገኙት ወለድ ሊከፈልበት የሚገባው ግብር 5% ወይስ 10% ነው? የሚል ጥያቄ ይነሳል። የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 56 ንኡስ አንቀጽ 1(ሀ) የእንግሊዝኛው ቅጂ 5% ግብር የሚከፈለው በኢትዮጵያ ነዋሪ በሆነ የፋይናንስ ተቋም ውስጥ በተቀመጠ ገንዘብ ላይ ሲሆን፤ በሌላ ማናቸውም ሁኔታ (ለምሳሌ በውጭ አገር በተቀመጠ ገንዘብ ላይ) 10% ግብር ሊከፈል እንደሚገባ ያመለክታል። ከላይ በተጠቀሰው የአንቀጹ የአማርኛ እና የእንግሊዝኛ ትርጉሙ መካከል ግልጽ የሆነ ቅራኔ ይታያል። የእንግሊዝኛው ቅጂ በኢትዮጵያ ነዋሪ በሆኑ ባንኮች ማስቀመጥን ለማበረታታት የተፈጠረ ልዩነት ነው እንዳይባል በስራ ባህሪያቸው ምክንያት የውጭ አገር ገንዘብን በውጭ ባንኮች ከሚያስቀምጡ ባንኮች እና በአበዳሪዎች በተፈጠረ ጫና ምክንያት በልዩ ሁኔታ ከተፈቀደላቸው ውስን ድርጅቶች በስተቀር በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው በውጭ አገር ገንዘብ ማስቀመጥ አይችልም። ይህም በመሆኑ የእንግሊዝኛው አንቀጽ ዓላማ በአገር ውስጥ ማስቀመጥን ለማበረታታት ነው የሚባል አይሆንም። ከዚህም በላይ በሕግ አተረጓጎም ሥርዓት መሠረት የዚህ ዓይነቱ መቃረን ሲኖር ተፈፃሚ ሊሆን የሚገባው ፓርላማው የተወያየበት የአማርኛው ቅጂ ነው። ከላይ የተጠቀሰው አንቀጽ የአማርኛ ቅጂ ልዩነት ያደረገው ወለዱን ያገኘው ሰው በኢትዮጵያ ነዋሪ በመሆኑ ወይም ባለመሆኑ ላይ ነው። ገንዘቡ የተቀመጠው በኢትዮጵያ በመሆን ያለመሆኑ ረገድ በአማርኛው ቅጂ የተደረገ ልዩነት የለም። በመሆኑም በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆኑ ባንኮች ከኢትዮጵያ ውጪ ባሉ የፋይናንስ ተቋማት ገንዘብ በማስቀመጥ የሚያገኙት ወለድ ሊከፈልበት የሚገባው ግብር 5% ይሆናል።

የገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 64(3) በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ሰው ከውጭ አገር ያገኘው የወለድ ገቢ በውጭ አገር ግብር የተከፈለበት ከሆነ በዚሁ ገቢ ላይ በውጭ አገር የከፈለው ግብር ከዜሮ በታች ሳይወርድ ተቀናሽ እንዲሆን ይፈቅዳል። በመሆኑም ባንኮች ከውጭ አገር ባገኙት የወለድ ገቢ ላይ በውጭ አገር የከፈሉት ግብር ካለ በተጠቀሰው አንቀጽ ወይም ገቢው ከተገኘበት አገር ጋር ከተደራራቢ ግብር ነፃ ለመሆን የሚያስችል ስምምነት የተፈረመ ከሆነ በስምምነቱ መሰረት ተቀናሽ ለመጠየቅ ይችላሉ።

1.22 <u>የካዝና መጠባበቂያ ገንዘብ</u>

ገንዘብ ያገኙ በየቀኑ ገንዘብ በመቀበል እና በመክፈል ሂደት ሊያጋማቸው ለሚችል የገንዘብ ጉድለት የጥሬ ገንዘብ መጠባበቂያ ይሰጣቸዋል።በባንኮቹ አሰራር መሰረት በየቀኑ የሚያዘው መጠባበቂያ በተቀናሽ ወጪነት የሚመዘገብ ሲሆን፤ የገንዘብ ጉድለት ሊያጋጥም የተያዘው የመጠበቂያ ሂሳብ ለጉድለቱ ማካካሻ ይውላል፤ ጉድለት ካላጋጠመ ወይም ለማካካሻ ያልዋለ ካለ የመጠባበቂያው ገንዘብ ለገንዘብ ያገኙ ይከፈላል። ጥያቄ ሆኖ የቀረበው ለካዝና መጠባበቂያ የተያዘው ገንዘብ ለማካካሻ ከመዋሉ በፊት ወይም ጉድለት ባለማጋጠሙ ለገንዘብ ያገኙ ከመከፈሉ በፊት በወጪነት ሊያዝ ይችላል ወይ? ለሰራተኛው ከተከፈለ የስራ ግብር ሊከፈልበት አይገባም ወይ? የሚል ነው።

ጉድለት ካላጋጠመ ወይም ለማካካሻ ያልዋለ ካለ የመጠባበቂያው ገንዘብ ለገንዘብ ያዦች ይከፈላል። ጥያቄ ሆኖ የቀረበው ለካዝና መጠባበቂያ የተያዘው ገንዘብ ለማካካሻ ከመዋሉ በፊት ወይም ጉድለት ባለማጋጠሙ ለገንዘብ ያዦች ከመከፈሉ በፊት በወጪነት ሊያዝ ይችላል ወይ? ለሰራተኛው ከተከፈለለት የስራ ግብር ሊከፈልበት አይገባም ወይ? የሚል ነው።

ለካዝና መጠባበቂያ የሚያዘው ገንዘብ ለግብር አከፋፈል ስሌት በወጪነት ሊያዝ የሚችለው ለማካካሻ ከዋለ ወይም ጉድለት ባለማጋጠሙ ለገንዘብ ያዦች ከተከፈለ በኋላ ነው። የዚህ ዓይነቱ ሂሳብ ወጪ ከመደረጉ በፊት በወጪነት እንዲያዝ የሚፈቅድ ሕግ የለም። በሚኒስትሮች ምክር ቤት የገቢ ግብር ደንብ አንቀጽ 65 (1) (ነ) ገንዘብ በሚቆጠርበት ጊዜ ለሚደርሰው ጉድለት ማካካሻ በሚሆን መጠን ብቻ ቀጣሪው ለተቀጣሪው የሚከፍለው እና ለዚሁ ዓላማ መዋሉ የተረጋገጠ የጥሬ ገንዘብ ማካካሻ ክፍያ በመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ከሚከፈል ግብር ነፃ መሆኑ ተመልክቷል። በመሆኑም የዚህ አይነቱ ክፍያ ከግብር ነፃ ሊደረግ የሚችለው ገንዘቡ ላጋጠመ ጉድለት ማካካሻ መዋሉ ሲረጋገጥ ብቻ ነው። የገንዘብ ጉድለት ባለማጋጠሙ የመጠባበቂያው ገንዘብ ለሠራተኛው የሚከፈል ከሆነ፤ ሠራተኛው ከመቀጠር ያገኘው ገቢ ስለሚሆን በደመወዙ ላይ ተደምሮ ግብር ሊከፍልበት ይገባል። አሰሪው በዚህ መልክ ያወጣው ወጪ ተቀናሽ ሊደረግለት የሚችለውም ከሠራተኛው ላይ ግብር ቀንሶ ገቢ ማድረጉ ሲረጋገጥ ይሆናል።

1.23 <u>ወደ ገንዘብ የሚለወጥ የአመት የዕረፍት ፈቃድ</u>

አንዳንድ ድርጅቶች ሠራተኞቻችን በዓመት የዕረፍት ፈቃዳቸው ላይጠቀሙ ይችላሉ በሚል ምክንያት የፈቃዱን ጊዜ ወደገንዘብ በመለወጥ በወጪነት የሚይዙ ሲሆን፤ ሰራተኛው እረፍት ያለመውጣቱ አልተረጋገጠም በሚል ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ግብሩን ቀንሰው ገቢ አያደርጉም።

በመሠረቱ የዚህ ዓይነቱ ሂሳብ በወጪነት ሊያዝ የሚገባው ሠራተኛው በዓመት የዕረፍት ፈቃዱ ለመጠቀም ያለመቻሉ ተረጋገጦ የዓመት ፈቃዱ በገንዘብ ተለውጦ ሊከፈለው እና ከዚህ ገንዘብ ላይ ግብር ተቀንሶ ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ሲደረግ ነው። ቀጣሪው ሊኖርበት የሚችለውን ወጪ በማሰብ ለጥንቃቄ ሲባል መዝግቦ መያዙ ከቀጣሪው አንጻር ተገቢ ሊሆን ቢችልም ወደመጠባበቂያ ሂሳብ እንዲዘዋወር በሕግ ከተፈቀደው በስተቀር ሌላ ማናቸውንም ሂሳብ በመጠባበቂያነት መያዝ አይቻልም።

በተጨማሪም በሕግ ነፃ ከተደረጉት በስተቀር ቀጣሪ ለተቀጣሪ የሚፈጽመው ክፍያ በወጪነት ሊያዝ የሚችለው ክፍያው በሠራተኛው ደመወዝ ላይ ተደምሮ ግብር የተከፈለበት መሆኑ ሲረጋገጥ ነው። በመሆኑም የዚህ ዓይነቱ ገቢ ከግብር ነፃ ሰላልሆነ ወጭው በተቀናሽነት የሚያዘው ከሰራተኛው ግብሩ ተቀንሶ ገቢ ሲደረግ ይሆናል።

1.24 <u>በህይወት መድን ስራ ላይ የተሰማሩ ግብር የሚከፈልበት ገቢ</u>

የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 አንቀጽ 47 የህይወት መድህን በመስጠት ስራ የተሰማሩ ድርጅቶች ግብር የሚከፈልበት ገቢ የሚሰላበትን ቀመር ይደነግጋል። በዚህ ቀመር ከተካተቱት አንዱ የኢንቬስትመንት ገቢ ሲሆን፤ የኢንቬስትመንት ገቢ ከሚባሉት መካከል የወለድ፤ የአክስዮን ትርፍ ድርሻ ወ.ዘ.ተ ይገኙበታል። በዚህ ረገድ ጥያቄ የሆነው በሠንጠረዥ 'መ' ስር ባሉት የወለድ እና የዴቪደንድ ገቢዎች ላይ የሚከፈለው ግብር የመጨረሻ በመሆኑ ከእነዚህ የሚገኘው ገቢ በሠንጠረዥ 'ሐ' ውስጥ እንዴት ሊካተት ይችላል የሚል ነው።

በሠንጠረዥ "መ" ስር ባሉት የወለድ እና የዴቪደንድ ገቢዎች ላይ የሚከፈለው ግብር የመጨረሻ መሆኑ ግልጽ ነው። ይሁን እንጂ አንድ ግብር ከፋይ እነዚህን ገቢዎች በንግድ ስራ ገቢው ውስጥ አካቶ ገቢ ቢያገኝ ባገኘው ገቢ ላይ ግብር መክፈል አለበት።በተመሳሳይ በህይወት መድን ስራ የተሰማራ ግብር ከፋይ የሚያገኘው የወለድ እና የዴቪደንድ ገቢ በሰንጠረዥ 'መ' መሠረት የሚከፈልበት ግብር የመጨረሻ ነው። ሆኖም ይህንን የወለድ እና የዴቪደንድ ገቢ ተጠቅሞ የህይወት መድን ስራ በመስራት የሚያገኘው ገቢ ግብር ይከፈልበታል። የተጠቀሰው አንቀጽ ይህንን የሚያስረዳ እንጂ የወለድ ወይም የዴቪደንድ ገቢ በድጋሚ ታክስ እንዲከፈልበት የሚያደርግ አይደለም።

1.25 <u>የጋራ ልማት ድርጅት (joint Venutre) የግብር አከፋፈል</u>

ለአንድ የተወሰነ ተግባር የሚቋቋሙ የጋራ ልማት ድርጅቶች ለምሳሌ ያላቸውን እውቀት፤ሃብት እና ልምድ አቀናጅተው በጨረታ በመሳተፍ አሸናፊ ሆነው አንድን ፕሮጀክት የሚገነቡ ድርጅቶች ግብር የሚከፍሉት በጋራ ባቋቋሙት ድርጅት ነው ወይስ በተናጠል? የሚል ጥያቄ ይነሳል።

የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 2(5) "ድርጅት" ማለት ኩባንያ፤የሽርክና ማህበር፤የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የመንግሥት የፋይናንስ ድርጅት ወይም በኢትዮጵያ ወይም በሌላ አገር ሕግ መሠረት የተመሠረተ የሰዎች ድርጅት መሆኑን ይደነግጋል። በዚህ የሀጉ ድንጋጌ መሰረት የሰዎች ድርጅት (association of persons) ለድርጅት በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የሚካተት ነው።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ የንግድ ሕግ አንቀጽ 234 joint venture ስሚለው የእሽሙር ማህበር የሚል ትርጉም የሚሰጥ ሲሆን፤ የዚሁ ሕግ አንቀጽ 235 የማህበሩ መኖር በሶስተኛ ወገኖች ከታወቀ ከዚያ ጊዜ አንስቶ ማህበሩ ከእነዚህ ወገኖች ጋር በሚኖረው ግንኙነት እንደ ህብረት ሽርክና ማህበር እንደሚቆጠር ይደነግጋል። በንግድ ሕግ

አንቀጽ 183 እንደተመለከተው የህብረት ሽርክና ማህበር እያንዳንዱ ማህበርተኛ ለማህበሩ ግዴታዎች ከማህበሩ ጋር በአንድነት እና በነጠላ ኃላፊ የሚሆንበት የንግድ ማህበር ነው። በንግድ ሕጉ አንቀጽ 175 መሰረት የሽርክና ማህበር በንግድ መዝገብ እንደተመዘገበ የህግ ሰውነት ያገኛል።

ከእነዚህ የሕጎቹ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው የጋራ ልማት ድርጅት (joint venture) በሚል የተለመደ አጠራር ተቋቁመው ከሶስተኛ ወገኖች ጋር ውል በመዋዋል የተለያዩ ስራዎችን የሚሰሩ ድርጅቶች በህጉ የህበረት የሽርክና ማህበር በሚል የሚታወቁ ሲሆን የሕግ ሰውነት አላቸው። በመሆኑም በገቢ ግብር አዋጁ መሠረት ድርጅት በሚል የሚታወቁ ሲሆን፤ የግብር ውሳኔ ሊሰጥ የሚገባው በድርጅቱ ስም ነው። ሆኖም በንግድ ሕጉ እንደተመለከተው ማህበርተኞቹ የአንድነት እና የነጠላ ኃላፊነት ያለባቸው በመሆኑ የታክሱ ባለስልጣን ሊከፈል የሚገባውን ግብር ከማህበርተኞቹ በጋራ ወይም ከእያንዳንዳቸው በተናጠል ለመጠየቅ ይችላል።

1.26 <u>በሳተላይት ቴሌቪዥን አገልግሎት ላይ የሚከፈል ግብር</u>

የሳተላይት ቴሌቪዥን አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች በሚያገኙት ገቢ ላይ ሊከፍሉ የሚገባው የሮያልቲ ግብር ወይስ የንግድ ትርፍ ግብር ነው? የሚል ጥያቄ ይነሳል።

በገቢ ግብር አዋጅ አንቀጽ 2(20) እንደተተረጎመው "ሮያልቲ" ማንኛውም የሥነ-ጽሁፍ፤ የሥነ-ጥበብ ወይም የሳይንሳዊ ስራ የቅጂ መብት ነው። በመሆኑም የእነዚህ መብቶች ባለቤት የሆነ በኢትዮጵያ ነዋሪ የሆነ ወይም በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነ ሰው ከሌሎች መካከል፤ ከቴሌቪዥን ጋር ተያይዞ በሳተላይት ወይም በሌላ ተመሳሳይ ቴክኖሎጂ የሚተላለፉ ወይም የሚታዩ ምስሎችን ወይም ድምፆችን ወይም ሁለቱንም ለመቀበል የሚያስችል መብት ለመስጠት የሚያስከፍለው ክፍያ እንደሁኔታው በአዋጁ አንቀጽ 51፤ 52፤ ወይም 54 መሠረት ግብር ይከፈልበታል።

በሳተላይት ቴሌቪዥን አገልግሎት በዋንኛነት ሁለት ግብይቶች ይኖራሉ። የመጀመሪያው የሥነ-ጽሑፍ፤ የሥነ-ጥበብ ወይም የሳይንሳዊ ስራው የቅጂ መብት ባለቤት የሳተላይት ቴሌቪዥን ኩባንያው የፈጠራ መብቱን ተቀብሎ ለማሰራጨት የሚያስችል ፈቃድ በመስጠት የሮያልቲ ገቢ የሚያገኝበት ሲሆን፤ ሁለተኛው የሳተላይት ቴሌቪዥን ኩባንያው ባለቤት ለደንበኞቹ የቴሌቪዥን አገልግሎት በመስጠት የንግድ ስራ ገቢ የሚያገኝበት ነው።

የፈጠራው ባለቤት የፈጠራ መብቱን ተቀብሎ ለማሰራጨት የሚያስችል ፈቃድ ለቴሌቪዥን ኩባንያው በመስጠት የሚያገኘው የሮያልቲ ገቢ ከላይ እንደተገለጸው

እንደሁኔታው በአዋጁ አንቀጽ 51፤ 52 ወይም 54 ግብር የሚከፈልበት ሲሆን፤ የሳተላይት ቴሌቪዥን አገልግሎት የሚሰጠው ኩባንያ የተከራየውን መብት በመጠቀም ለደንበኞች የሚሰጠው የቴሌቪዥን አገልግሎት በሠንጠረዥ "ሐ" መሠረት የንግድ ትርፍ ግብር ሊከፈልበት ይገባል።

1.27 በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚሰሩ የውጭ አገር ባለሙያዎች የግብር ነፃ መብት

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ የሚሰሩ የውጭ አገር ባለሙያዎች በመቀጠር በሚያገኙት ገቢ ላይ እስከ 5 ዓመት ለሚደርስ ጊዜ ከግብር ነፃ እንደሚሆኑ በኢንዱስትሪ ፓርክ አዋጅ የተመለከተ ሲሆን፤ በሌላ በኩል በገቢ ግብር ደንብ አንቀጽ 54(1) (ሀ) በወጪ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች ለእውቀት ሽግግር ከውጭ አገር የሚቀጥሩዋቸው ባለሙያዎች እስክ 5 ዓመት ለሚደርስ ጊዜ በመቀጠር የሚያገኙት ገቢ ከግብር ነፃ እንደሚሆን የተመለከተ በመሆኑ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ የሚሰሩ ሁለቱንም መብቶች መጠቀም የሚችሉ ስለመሆኑ ጥያቄ ተነስቷል።

በሁለቱም ሕጎች ማበረታቻው የተፈቀደው በወጪ ንግድ ስራ ላይ የተሰማሩ ባለሀብቶች ምርታቸው ጥራቱን የጠበቀ ሆኖ በአለም አቀፍ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆን በማስቻል የአገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ገቢ ለማሳደግ ነው። በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥ ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መብቱ የተፈቀደው በወጪ ንግድ ስራ ላይ የሚሰማሩ ስለሆነ ብቻ ነው። በመሆኑም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ውስጥም ሆነ ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጪ ለወጭ ንግድ የሚውሉ ዕቃዎችን የሚያመርት ባለሀብት የሚቀጥራቸው የውጭ አገር ባለሙያዎች በመቀጠር የሚያገኙት ገቢ ከግብር ነፃ ሊሆን የሚችለው ከ5 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ብቻ ነው።

1.28 የግብር ዕዳ ያለባቸው ታክስ ከፋዮች የሚያቀርቡት የተመላሽ ጥያቄ

ግብር ከፋዮች በተወሰነባቸው ግብር ቅር በመሰኘት አቤቱታቸውን በተለያየ ደረጃ ላሉ የፍትህ አካላት አቅርበው ጉዳዩ በመታየት ላይ እያለ በሌላ የታክስ ጉዳይ ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለ ታክስ ተመላሽ እንዲመለስላቸው ጥያቄ ያቀርባሉ።

በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 50 እንደተደነገገው ሊከፈል ከሚከፈለው በላይ የተከፈለ ታክስ ተመላሽ ሊደረግ የሚችለው በብልጫ የተከፈለው ታክስ በንኡስ አንቀጽ 4 በተዘረዘረው መሰረት ግብር ከፋዩ ለሚፈለግበት ታክስ ክፍያ እንዲውል ከተደረገ በኋላ ተራፊ ሂሳብ ያለ እንደሆነ ነው።

በመሆኑም ለግብር ከፋዩ ተመላሽ የሚደረግ ሊከፈል ከሚገባው በላይ የተከፈለ ታክስ ያለ እና ግብር ከፋዩ ከወለድ እና መቀጫ ለመዳን ይህ ተመላሽ ሂሳብ ለሚፈለግበት የግብር እዳ እንዲውል ለማድረግ የተስማማ ከሆነ ተመላሹን ለእዳው ማካካሻ ማዋል ይቻላል። ግብር ከፋዩ በአቤቱታው መቀጠል ከፈለገ ግን ጉዳዩ እልባት ሳያገኝ ተመላሹን መክፈል የሚቻል አይሆንም።

1.29 በተጨማሪ እሴት ታክስ ደረሰኝ ለማሕበራዊ ጉዳዮች የሚሰበሰብ ገንዘብ

አንዳንድ ግብር ከፋዮች ለህብረተሰቡ በሚያቀርቡት ዕቃ ወይም አገልግሎት ዋጋ ላይ ለበጎ አድራጎት የሚውል የተወሰነ ገንዘብ በማከል ሽጠው ገንዘቡን ለበጎ አድራጎት ዓላማ ካዋሉ በኋላ ገንዘቡ ለበጎ አድራጎት የተሰበሰበ ስለሆነ ግብር ሊከፈልበት አይገባም የሚል ጥያቄ ያቀርባሉ።

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ እንደተደነገገው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ስሌት መሠረት የሚሆነው ዕቃው ወይም አገልግሎቱ የተሸጠበት ዋጋ ሲሆን፤ ከዚህ ዋጋ ላይ የሚቀናነስ ገንዘብ ሊኖር አይችልም። በመሆኑም ከዕቃው ዋጋ ውስጥ የተወሰነው ለበጎ አድረጎት የሚውል ስለሆነ ግብር ሊከፈልበት አይገባም የሚለው መከራከሪያ ተቀባይነት የለውም።

ግብር ከፋዩ ለበጎ አድራጎት የሚውል ገንዘብ ለማሰባሰብ በሕግ መሠረት (በሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ አንቀጽ 49(1)) ፈቃድ ያገኘ ከሆነ ለዚሁ ዓላማ የሚውል ደረሰኝ በማሳተም ከሚሰበሰብ በስተቀር ከዕቃው ዋጋ ውስጥ የተወሰነው ለበጎ አድራጎት ተግባር የሚውል ነው ሊል አይችልም።

1.30 ለጤና ባለሙያዎች የሚፈጸም የተረኝነት የተጋላጭነትና የሌሎች አበሎች ክፍያ

ለጤና ባለሙያዎች የሚፈጸም የተረኝነት የተጋላጭነትና የሌሎች አበሎች ክፍያ ላይ ስለሚከፈለው ግብር ማብራሪያ እንዲሰጥ ጥያቄ ይቀርባል።

በገቢ ግብር አዋጅ በተደነገገው መሰረት ከግብር ነጻ እንዲሆኑ በአዋጁ እና በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ከተፈቀደው በስተቀር በመቀጠር የሚገኝ ገቢ ግብር ሊከፈል ይገባል። በመሆኑም ከተጋላጭነት አበል በስተቀር ሌሎች ከግብር ነጻ ያልተደረጉ አበሎች ግብር ይከፈልባቸዋል።

ይህም በመሆኑ የገንዘብ ሚኒስቴር ባስተላለፈው መመሪያ የጤና ተቋማት በጀት በሚጠይቁበት ጊዜ ሊከፈል የሚገባውን ግብር ጭምር ከግምት ውስጥ በማስገባት ጥያቄያቸውን ማቅረብ እንደሚገባቸው ገልጿል። በመሆኑም የበጀት ጥያቄው ለሠራተኛው የሚከፈለውን የተጣራ ክፍያ እና በዚህ ገቢ ምክንያት ሰራተኛው የሚከፍለውን ግብር ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት።

2. <u>የኤክሳይዝ ታክስን በሚመለከት የሚነሱ አከራካሪ ጉዳዮች</u>

2.1 <u>ተመላሽ ለሚደረግ ጠርሙስ የወጣ የትራንስፖርት ወጪ በማምረቻ ወጪ ውስጥ የሚካተት መሆን ያለመሆኑ</u>

በተሻረው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሰረት የማምረቻ ወጪ በመሆኑ፣ አዲሱ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በተመረቱ መጠጦች ላይ የሚከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ በሚሠላበት ጊዜ ተመላሽ ለሚደረግ ጠርሙስ የወጣ የትራንስፖርት ወጪ በማምረቻ ወጪ ውስጥ መካተት አለበት ወይስ የለበትም? የሚል አከራካሪ ጥያቄ ይነሳል።

በማምረቻ ወጪ ውስጥ ሊካተት ይገባል የሚለውን ሃሳብ የሚያነሱት መከራከሪያ ነጥብ አድርገው የሚያቀርቡት ፋብሪካው አዲስ ጠርሙስ ገዝቶ ወደፋብሪካው ለማጓጓዝ የሚያወጣው የትራንስፖርት ወጪ የማምረቻ ወጪ እስከተባለ ድረስ ተመላሽ የሚደረገውን ጠርሙስ ለማጓጓዝ የሚወጣው ወጪም የማምረቻ ወጪ ሊባል ይገባል የሚል ነው።

የዚህ ዓይነቱ የመከራከሪያ ሀሳብ በተወሰነ ደረጃ እውነትነት ያለው ቢሆንም ጠርሙሱ ተመላሽ ባይደረግ በማምረቻ ወጪ ውስጥ የሚካተት የትራንስፖርት ወጪ ስለማይኖር በአንድ ጊዜ የተመረቱ ምርቶች የማምረቻ ወጪ እንዲለያይ ማድረግ አስቸጋሪ በመሆኑ ለታክሱ አስተዳደር ቀላልነት አፈፃፀሙን ወጥ ማድረግ ተገቢ ይሆናል። ከዚህም በተጨማሪ የኤክሳይዝ ታክስ የስሌት መሠረት የማምረቻ ወጪ እንደሆነ የሚያዘው አዋጅ የተሻረና የስሌቱ መሠረት የማምረቻ ወጪ እንዲሆን የማድረጉ አሰራር የሚያገለግለው ከአዲሱ አዋጅ በፊት ለነበረ የኤክሳይዝ ታክስ አፈፃፀም ብቻ ነው።

በመሆኑም ለፋብሪካው ተመላሽ የሚደረግን ጠርሙስ ለማጓጓዝ የሚወጣ የትራንስፖርት ወጪ በማምረቻ ወጪ ውስጥ እንዳይካተት ማድረግ የተሻለ አማራጭ ሆኖ ተገኝቷል።

2.2 <u>ለጠርሙስ መግዣ የወጣ ወጪ አያያዝ</u>

የኤክሳይዝ ታክስ በማምረቻ ወጪ ላይ ይሰላ በነበረበት ጊዜ ለጠርሙስ መግዣ የወጣን ወጪ አንዳንድ ድርጅቶች ሙሉ በሙሉ በተገዛበት አመት በወጪነት የሚይዙ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ ቋሚ ንብረት አድርገው በመመዝገብ የእርጅና ቅናሽ እንዲሰላበት ስለሚያደርጉ አፈጻጸሙ ወጥነት አልነበረውም።

ጠርሙስ ከአንድ ዓመት በላይ አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል ሲሆን፤ ጥቅል ዋጋውም ከብር 2000 በላይ በመሆኑ ለታክስ አስተዳደሩ አመቺነት በቋሚ ንብረትነት መመዝገቡ ተገቢ ሆኖ ታይቷል። በተሻረው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ለማምረቻ ወጪ በተሰጠው ትርጉም ውስጥ የማይካተተው የማሽነሪ የእርጅና ቅናሽ ነው። በመሆኑም የሌሎች ቋሚ ንብረቶች የእርጅና ቅናሽ በማምረቻ ወጪ ውስጥ ተካቶ የኤክሳይዝ ታክስ መሰረት ሊሆን ይገባል። በዚህም መሰረት ለጠርሙስ መግዣ የወጣ ወጪ ለዓመታት ተከፋፍሎ የሚሰላው የእርጅና ቅናሽ የማምረቻ ወጪ ውስጥ ሊካተት ይገባል።

2.3. <u>የኤክሳይዝ ታክስ ደረሰኝ አሰጣጥ</u>

የኤክሳይዝ ታክስ የሚሰበሰበው በማምረቻ ቦታ ሲሆን፤ ግብይት በሚካሄድበት ጊዜ የተሰበሰበው የኤክሳይዝ ታክስ በደረሰኝ ላይ መታየት እንደሚገባው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ይደነግጋል። ይሁን እንጂ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈልባቸውን እቃዎች የሚያመርቱ አንዳንድ ፋብሪካዎች ምርታቸውን ለገበያ የሚያቀርቡት ከፋብሪካው ርቆ በሚገኝ የመሸጫ መጋዘን ወይም በየደንበኞቻቸው የንግድ ቦታ በመሄድ በመሆኑ አስቀድሞ ደረሰኝ ለመቁረጥ ገዢውን ስለማያውቁ ደረሰኙ በምን መንገድ እንደሚቆረጥ ጥያቄ ያቀርባሉ።

ይህ ጥያቄ ከዚህ ቀደም ቀርቦ ማበራሪያ የተሰጠበት ቢሆንም በድጋሚ የሚቀርብ በመሆኑ አፈጻጸሙን ግልጽ ለማድረግ ተጨማሪ ማብራሪያ መስጠት አስፈላጊ ሆኗል። የኤክሳይዝ ታክስ የመክፈል ግዴታ የሚቋቋመው ምርቱ ከፋብሪካ በሚወጣበት ጊዜ ሲሆን፤ የተሰበሰበው ታክስ ለታክሱ ባለስልጣን ገቢ የሚደረገው ምርቱ ከፋብሪካ በወጣ በ30 ቀን ጊዜ ውስጥ ነው። አምራቹ ምርቱን ለገበያ የሚያቀርበው ከፋብሪካው ርቆ በሚገኝ የመሸጫ መጋዘን ውስጥ ከሆነ ምርቱ ከፋብሪካ ሲወጣ የማስረከቢያ ሰነድ (delivery note) መቁረጥ ያለበት ሲሆን፤ ምርቱ ከፋብሪካው በወጣ በ30 ቀን ውስጥ ምርቱን ለሽያጭ በማዋል ደረሰኝ ቆርጦ የሰበሰበውን ታክስ ለግብር አስገቢው መስሪያ ቤት ገቢ ማደረግ አለበት።

ፋብሪካው ያመረተውን ምርት በየቀኑ ከፋብሪካው በማውጣት በከተማ ውስጥ በተሽከርካሪ በማዞር ለደንበኞች የሚሸጥ ከሆነ ምርቱ ከፋብሪካው ሲወጣ የማስረከቢያ ሰነድ (delivery note) መቆረጥ ይኖርበታል። ሽያጩ በሚከናወንበት ጊዜም ደረሰኝ መቆረጥ ያለበት ሲሆን፤ በእለቱ ለሽያጭ ያልዋለው ምርት ወደፋብሪካው ሲመለስ የመረከቢያ ሰነድ (store receiving note) መቆረጥ አለበት።

የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሰረት የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ መሆኑ በአዋጁ በግልጽ የተመለከተ ስለሆነ ከዚህ በላይ በተመለከተው ሁኔታ ከፋብሪካ ውጭ የሚሸጡ ምርቶች የኤክሳይዝ ታክስ ስሌት መሰረትም የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ነው።

2.4 <u>በግብዓት ላይ የተከፈለ ታክስ ተቀናሽ የሚደረግበት አፈፃፀም</u>

በኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ እንደተደነገገው በአልኮል፣ ትምባሆ እና ስኳር ላይ ከሚከፈለው በስተቀር በሌሎች በግብዓትነት የሚያገለግሉ ምርቶች ላይ የተከፈለ የኤክሳይዝ ታክስ በመጨረሻው ምርት ላይ ከሚከፈለው ታክስ ጋር እንዲቀናነስ ይደረጋል። ጥያቄ ሆኖ የቀረበው ተመላሽ (rebate) የተፈቀደለት ግብአት ወደአገር በሚገባ ጊዜ የሚከፈለው የጉምሩክ ቀረጥና ታክስ ለገቢ ግብር አከፋፈል በወጪነት ይያዛል ወይስ አይያዝም? የሚለው ነው።

በመጀመሪያ ፋብሪካው በግብአቱ ላይ ለጉምሩክ ኮሚሽን የከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ በተሰብሳቢነት (receivable) መያዝ አለበት። ከዚህ በኋላ ይህንን ግብዓት ተጠቅሞ ባመረተው ምርት ላይ የኤክሳይዝ ታክሱን በሚሰበስብበት ጊዜ በደረሰኙ ላይ ከታየው የተሰበሰበ የኤክሳይዝ ታክስ ላይ ወደአገር በገባው ግብዓት ላይ የከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ መጠን በመቀነስ በልዩነት የሚታየውን ሂሳብ ብቻ ለታክሱ ባለሥልጣን ገቢ ማድረግ አለበት።አዲሱ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ የኤክሳይዝ ታክስ በሚከፈልባቸው ዕቃዎች ላይ የሚሰበሰበው ታክስ በደረሰኝ ላይ መታየት እንደሚገባው የደነገገው ለዚህ አፈጻጸም ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ነው።

በመሆኑም የዚህ ዓይነቱ ግብር ከፋይ ግብዓቱን ወደ አገር ሲያስገባ የከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ በወጪነት ሊያዝ የሚችል አይሆንም። በግብዓት ላይ የከፈለው የኤክሳይዝ ታክስ ተመላሽ እንዲደረግ ያልተፈቀደለት ግብር ከፋይ ግን ለጉምሩክ ኮሚሽን የከፈለውን የኤክሳይዝ ታክስ በወጪነት ሊይዝ ይችላል።

2.5 <u>ለጨርቃጨርቅ ማምረቻ ስለሚውሉ ግብአቶች እና የስፌት አገልግሎት</u>

ለጨርቃጨርቅ ማምረቻ በሚውሉ እንደ ክር፣ ድር እና ማግ ባሉ ግብአቶች እንዲሁም በልብስ ስፌት አገልግሎት ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈል ስለመሆን ያለመሆኑ በተደጋጋሚ ጥያቄ ይቀርባል።

ከኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ጋር በተያያዘው ሰንጠረዥ እንደተመለከተው በጨርቃጨርቅ ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ተጥሏል፣ ከዚህ ውጪ ለጨርቃጨርቅ ማምረቻ በሚውሉ ግብአቶች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ያልተጣለ በመሆኑ የኤክሳይዝ ታክስ አይከፈልባቸውም። ከዚህ ጋር አብሮ የሚነሳው በጨርቃጨርቅ እና በአልባሳት ላይ

የተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ተፈጻሚ የሚሆነው በየትኛው ደረጃ ባሉ አምራቾች ላይ ነው? የሚል ጥያቄ ይነሳል። በኤክሳይዝ አዋጅ እንደተደነገገው በጨርቃጨርቅ እና በአልባሳት ላይ የተጣለው የኤክሳይዝ ታክስ ተፈጻሚ የሚሆነው በፋብሪካ ደራሽ በሚመረተው ላይ ብቻ ነው። በመሆኑም "ፋብሪካ" የሚለው ቃል የገንዘብ ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ መተርጎም አለበት።

በሌላ በኩል በሰንጠረዡ በአልባሳት (garment) ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የተጣለ መሆኑ የተገለጸ ሲሆን፤ በልብስ ስፌት አገልግሎት ላይ ግን የኤክሳይዝ ታክስ አልተጣለም። በመሆኑም ከደንበኞች የሚቀርብላቸውን ጨርቅ የመስፋት አገልግሎት የሚሰጡ ግብር ከፋዮች የኤክሳይዝ ታክስ እንዲከፍሉ ሊጠየቁ አይችልም።

2.6 በባለሥስት እግር ተሽከርካሪዎች ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ

ቀደም ሲል ስራ ላይ በነበረው የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ማሻሻያ ቁጥር 307/1994 መሰረት ወደ አገር በሚገቡ እና አገር ውስጥ በሚመረቱ በባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ የሚከፈል ስለመሆኑ ጥያቄ ይነሳል።

የገንዘብ ሚኒስቴር በ20/04/2004 በቁጥር ታክ/8/5/575 ባስተላለፈው መመሪያው ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች ህብረተሰቡን ከመኖሪያው አካባቢ መደበኛ ትራንስፖርት ወደሚገኝበት ቦታ በማጓጓዝና በገጠር አካባቢዎች ያለውን የትራንስፖርት ችግር በማቃለል ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸው መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት ለህዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች ወደአገር በሚገቡበት ጊዜ ከኤክሳይዝ ታክስ እና ከሱር ታክስ ነጻ እንዲሆኑ ወስኗል።

የተጠቀሰው መመሪያ በወጣበት ጊዜ ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎችን በአገር ውስጥ የሚገጣጥሙ ኢንዱስትሪዎች የሌሉ በመሆኑ መመሪያው ያተኮረው ወደአገር በሚገቡ ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች ላይ ነው። ይሁን እንጂ ወደአገር የሚገቡ ተሽከርካሪዎች ከቀረጥና ታክስ ነጻ ሆነው እንዲገቡ ተፈቅዶ ሳለ በአገር ውስጥ የሚመረቱት ታክስ እንዲከፈልባቸው ማድረግ ምንም አይነት የኢኮኖሚ ምክንያት አይኖረውም። በመሆኑም አዲሱ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ስራ ላይ እስከሚውልበት ጊዜ ድረስ ወደአገር ቢገቡም ሆነ አገር ውስጥ በተመረቱ ባለሦስት እግር ተሽከርካሪዎች ላይ የኤክሳይዝ ታክስ ሊከፈል አይገባም።

ከአዲሱ ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ጋር የተያያዘው ሰንጠረዥ ተራ ቁጥር 19.15 አዲስ ባለሶስት እግር ተሽከርካሪዎች ወደአገር ሲገቡም ሆነ በአገር ውስጥ ሲመረቱ 5%፤ ያገለገሉ ከሆነ ደግሞ እንደአገልግሎቱ መጠን ከፍ በሚል መጣኔ የኤክሳይዝ ታክስ

ሊከፈልባቸው እንደሚገባ ይደነግጋል። በመሆኑም አዲሱ የኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ስራ ላይ ከዋለበት ቀን ጀምሮ መመሪያው የተሻረ ስለሆነ ባለሦስት እግር ተሽከርካሪዎች የኤክሳይዝ ታክስ ሊከፈልባቸው ይገባል።

3. <u>የተጨማሪ እሴት ታክስ</u>

3.1 <u>በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው የሚሰጥ አገልግሎት</u>

በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው በተሰጠ አገልግሎት ምክንያት በቀጥታ በገዢው ለታክሱ ባለስልጣን የሚከፈለው የተጨማሪ እሴት ታክስ ተፈጻሚ የሚሆነው አገልግሎቱ የት ሲሰጥ ነው? የሚለው ጥያቄ አከራካሪ ሲሆን ይታያል።

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ ቁጥር 285/1994 አንቀጽ 4(7) በኢትዮጵያ ነዋሪ ባልሆነ ሰው የሚከናወኑ የእቃ እና አገልግሎት የመስጠት ስራዎች አዋጁ ተፈጻሚ የሚደረግባቸው በኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ በሆነ ድርጅት ወይም በኢንተርኔት የተከናወኑ ሲሆን ብቻ እንደሆነ ይገልጻል። ታክስ ስለመጣል የሚደነግገው የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 6 (3) እንዲሁም 6(2) (ለ) በአንቀጽ 8 ነጻ ከተደረጉት በስተቀር <u>በኢትዮጵያ ውስጥ</u> የሚቀርብ እቃ ወይም አገልግሎት ታክስ የሚከፈልበት እንደሆነ፤ በአንቀጽ 23 መሠረት ወደአገር በሚገቡ አገልግሎቶች ዋጋ ላይ በ15% የማስከፈያ ልክ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሊከፈል እንደሚገባ ይደነግጋል። በሌላ በኩል በገዥው ስለሚሰበሰብ ታክስ (Reverse Taxation) የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 23 በኢትዮጵያ ነዋሪ ያልሆነና ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገበ ሰው በኢትዮጵያ ውስጥ አገልግሎት የሰጠ እንደሆነ የተሰጠው አገልግሎት ታክስ የሚከፈልበት መሆኑን ይገልፃል።

ከተጠቀሱት የአዋጁ ድንጋጌዎች መረዳት እንደሚቻለው በገዢው የሚሰበሰበው ታክስ ተፈጻሚ የሚሆነው አገልግሎቱ የተሰጠው <u>በኢትዮጵያ ውስጥ</u> ሆኖ አገልግሎት ሰጪው በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ ያልሆነ ወይም ዘላቂ ድርጅት የሌለው ከሆነ ወይም አገልግሎቱ የተሰጠው ከኢትዮጵያ ውጪ በኢንተርኔት ሆኖ አገልግሎቱ ጥቅም ላይ የዋለው በኢትዮጵያ ውስጥ ሲሆን ነው።

የተጨማሪ እሴት ታክስ እቃው/አገልግሎቱ ጥቅም ላይ የዋለበትን አገር (destination principle) የሚከተል የፍጆታ ታክስ በመሆኑ እቃው/አገልግሎቱ ጥቅም ላይ የዋለው በኢትዮጵያ ውስጥ ካልሆነ በገዥው የሚሰበሰብ ታክስ አይኖርም።

3.2 <u>ከቀረጥ ነፃ ለሚገባ ተሽከርካሪ የሚከፈል ኮሚሽን</u>

የቀረጥ ነፃ መብት ያላቸው ድርጅቶች መኪና የማስመጣት ፈቃድ የሌላቸው በሚሆንበት ጊዜ ፈቃድ ያላቸውን ሰዎች በመጠቀም እና ኮሚሽን በመክፈል የቀረጥ ነጻ መብት ያገኙባቸውን ዕቃዎች ወይም ተሸርካሪዎች ያስመጣሉ።ከዚህ ጉዳይ ጋር ተያይዞ የሚከፈለው ኮሚሽን ተጨማሪ እሴት ታክስ ይመለከተዋል ወይስ አይመለከተውም የሚለው ሀሳብ አከራካሪ ሆኖ ቆይቷል።

በተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንቀጽ 4 እንደተመለከተው "አገልግሎት ማቅረብ" አንድን ተግባር ለመፈጸም የሚያስችሉ ነገሮችን ማመቻቸትን ይጨምራል። በመሆኑም የቀረጥ ነፃ መብት ያላቸው ሰዎች ወይም ድርጅቶች የቀረጥ ነጻ መብታቸውን መጠቀም እንዲችሉ ለማድረግ በኮሚሽን ወኪል ለተሰጠ ተሽከርካሪ የማስመጣት አገልግሎት የሚከፈል ኮሚሽን የተጨማሪ እሴት ታክስ ሊከፈልበት ይገባል።

3.3 <u>በመንቀሳቀስ ላይ ያለ ድርጅት ሲሸጥ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈፃሚ የሚደረግበት ሁኔታ</u>

የተጨማሪ እሴት ታክስ አዋጅ አንቀጽ 7(2) (መ) አንድ የተመዘገበ ሰው ለሌላ የተመዘገበ ሰው በነጠላ ግብይት የአንድን ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ወይም ራሱን ችሎ የሚሰራ ታክስ የሚከፈልበት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ክፍል አብዛኛውን ሀብት ላልተወሰነ ጊዜ ይንቀሳቀሳል ተብሎ ለተቋቋመ ድርጅት ያስተላለፈ እንደሆነ ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ እንደሚደረግ ይደነግጋል።

አዋጁ ይህንን የፈቀደው የንግድ ድርጅቶችን ከአንዱ ወደሌላው ለማስተላለፍ ተግባር ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር ሲሆን፤ በዚህ ሂደት ግን ተመላሽ የተደረገ በግብአት ላይ የተከፈለ ታክስ ቢኖር ታክሱ ከመጨረሻው ምርት ላይ ሳይሰበሰብ እንዳይቀር ቅድመ ሁኔታዎችን አስቀምጧል። በመሆኑም የዚህ ዓይነቱ ግብይት ዜሮ የማስከፈያ ልክ ተፈጻሚ ሊደረግለት የሚችለው የሚከተሉት ሲሟሉ ይሆናል።

- ሻጭ እና ገዥ ሁለቱም ለተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገቡ መሆን አለባቸው፤
- ግብይቱ በአንድ ጊዜ (በነጠላ) የተፈፀመ መሆን አለበት፤ በተለያየ ጊዜ የተፈፀሙ ግብይቶች ቢቀርቡ ተቀባይነት አይኖራቸውም፤
- የተሸጠው ድርጅቱ ሙሉ በሙሉ ወይም ከድርጅቱ ውስጥ አንድ ራሱን ችሎ የሚሰራ የስራ ዘርፍ አብዛኛው ሃብት መሆን አለበት፤የተናጠል መሣሪያ ሽያጭ ከሆነ ተቀባይነት ሊኖረው አይገባም፤

- የተሸጠው ድርጅት ከመሸጡ በፊት ሲያከናውን የነበረውን የስራ እንቅስቃሴ በመቀጠል ላልተወሰነ ጊዜ የሚሰራ መሆኑን የሚያረጋግጥ ማስረጃ መቅረብ አለበት፤
- የሽያጩ ውል ሽያጩ በተከናወነ በ21 ቀናት ውስጥ ለታክሱ ባለሥልጣን መቅረብ ያለበት ሲሆን፤ ከዚህ ጊዜ በኋላ የሚቀርብ ውል ተቀባይነት የለውም፤

4. <u>የታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 85 (ስህተትን ስለማረም)</u>

የታክሱ ባለሥልጣን በታክስ ሕጎች መሠረት ለታክስ ከፋዩ የሰጠው የታክስ ስሌት ማስታወቂያ ወይም ሌላ ሰነድ የጽሑፍ፤ የሂሳብ ስሌት ወይም ሌላ ማንኛውም ስህተት ያለበት ከሆነ ባለሥልጣኑ ስህተቱን ማረም እንደሚችል በታክስ አስተዳደር አዋጅ አንቀጽ 85 ተደንግጓል። ይሁን እንጂ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚታረመው በታክስ ሕግ ወይም በጉዳዩ ኩነቶች ላይ የትርጉም ጥያቄ ሊያስነሳ የሚችል መሆን የለበትም የሚለው የአንቀጹ ድንጋጌ አከራካሪ ሲሆን ይታያል።

የእነዚህ ሁለት የጥንቃቄ ሁኔታዎች (caveat) እንደምታ ምን እንደሆነ መረዳት በአንቀጹ መሰረት ግልጽ የሆኑ ስህተቶችን በቀላሉ በማረም በግብር ከፋዩ ላይ የሚደርሰውን እንግልት ማስቀረት ያስችላል። ለምሳሌ የታክስ ሕጎች ድንጋጌ ግልጽ ባለመሆኑ የተለያየ ትርጉም ሊሰጥ ይችላል። የዚህ ዓይነት አስቸጋሪ የትርጉም ጥያቄዎች መፈታት ያለባቸው የገንዘብ ሚኒስቴር በታክስ አስተዳደር አዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት የታክስ ሕጎችን አስቀድሞ እንዲተረጉም በማድረግ (advance ruling) ወይም በፍርድ ቤቶች በሚሰጥ አስገዳጅ ትርጉም ይሆናል። ሆኖም ለግብር ውሳኔው መሠረት የሆነው የታክስ ሕግ አንቀጽ ግልጽ ሆኖ ሳለ በተሳሳተ መንገድ በመረዳት ወይም አንቀጹን ያለአግባብ በመጠቀም የተሰጠ የግብር ውሳኔ ከሆነ የታክሱ ባለስልጣን የዚህ ዓይነቱን ስህተት ለማረም ይችላል።

በሌላ በኩል ለግብር ውሳኔው መሰረት የሆነው ኩነት (facts of the case) ስህተት ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ግብር ከፋዩን የማይመለከት ወይም ከስራ እንቅስቃሴው ጋር ያልተዛመደ መረጃን መሠረት በማድረግ ግብር ሊወሰን ይችላል። በመሆኑም መረጃው አግባብነት የሌለው ከሆነ ውሳኔው ስህተት በመሆኑ ሊታረም ይገባል። ሆኖም የመረጃው አግባብነት ወይም ትክክለኛነት አከራካሪ ከሆነ የግብር ሰብሳቢው እና/ወይም ግብር ከፋዩ በሚያቀርቡት ተጨማሪ መረጃ መረጋገጥ ሰላለበት የግብር ውሳኔው ስህተት ነው በሚል ወደማረም መሄድ አይቻልም።

ከዚህ አንፃር በታክስ ሕግ ወይም በጉዳዩ ኩነቶች ላይ የትርጉም ጥያቄ ተነሳ የሚባለው መቼ ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል። በገቢ ሰብሳቢው መሥሪያ ቤት ውስጥ ባሉ ባለሙያዎች/ኃላፊዎች መካከል የሀሳብ ልዩነት መፈጠሩ ተፈጥሮአዊ ነው። የዚህ ዓይነት ሁኔታ ሲያጋጥም የመሥሪያ ቤቱ አቋም ሆኖ መወሰድ ያለበት በየደረጃው ያለ ኃላፊ

የሚሰጠው ውሳኔ እንጂ አዲተሩ ወይም ባለሙያው በጉዳዩ ላይ ያለው አስተያየት/አቋም ሊሆን አይችልም። በመሆኑም ኃላፊው ስህተት አለ ብሎ በእርግጥ ካመነ እንደሁኔታው የስራ ክፍሉን ወይም ተቋሙን በየደረጃው የሚመራው እርሱ ስለሆነ ስህተቱ መታረም አለበት። ይሁን እንጂ የግብር አስገቢው መሥሪያ ቤቱ ኃላፊ ስህተት የለም ብሎ ካመነ ውሳኔው ሊለወጥ የማይችል ሲሆን በታክስ ከፋዩ ወይም በሌላ አካል የቀረበው የሕግ ወይም የፍሬነገር ጥያቄ በሕጉ የተዘረጋውን ሥርዓት በመከተል መፈታት አለበት።

ሌላው የሚነሳው ጥያቄ ስህተት ሊታረም የሚችለው ጉዳዩ በየትኛው ደረጃ ላይ በሚገኝበት ጊዜ ነው? የሚለው ነው። በግብር ጉዳይ ላይ የተነሳው ክርክር ለፍርድ ቤት ቀርቦ ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ የፍርድ ቤቱ ውሳኔ መታረም ያለበት የዳኝነት ሥርዓቱን ተከትሎ ነው። ከዚህ ውጪ ጉዳዩ በማንኛውም ደረጃ ላይ ባለበት ጊዜ የግብር አስገቢው ባለሥልጣን ስህተቱን ሊያርም ይችላል።